

# ተቀናቃኝ ቡድኖችና ፖለቲካ

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 3

በመስመር መካከል ምርጥ ሙዚቃና ምርጥ ሙዚቀኛ



ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም 11

ወጣቱን ከሱስ በመታደግ እናቶችን እንኳን አደረሳችሁ ብንላቸው ፤ እናቴ እንኳን አደረሰሽ እወድሻለሁ ! !



ግርማ ሠይፉ ማሩ 12



ቅፅ 5 ቁጥር 188 አርብ ግንቦት 10 2004 ዓ.ም www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ዋጋ 7.00 ብር

# ኢህአዴግ የማይሰማቸው የኢህአዴግ ድምፆች 5




## በግንቦት 7 ክስ የዕድሜ ልክ ፍርደኛ የነበሩት አቶ ክፍሌ ስንሻው አረፉ

*** <<ሞቱ ለእኛ በጣም ከባድ ጉዳት ነው>>** እህታቸው ወ/ት መቅደስ ስንሻው

በ2001 ዓ.ም. ‹‹ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል እና በትጥቅ አመፅ ለመጣል…››› በሚል በእነ ብ/ጄኔራል ተፈራ ማሞ የክስ መዝገብ በአቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል የዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው የነበሩት አቶ ክፍሌ ስንሻው ባጋጠማቸው ህመም ሳቢያ ለወራቶች በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ባለፈው ሳምንት አርብ ዕለት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

የማረሚያ ቤት የሕክምና መስጫ ተቋም በፃፈው ሪፈር መሰረት አቶ ክፍሌ በመጀመሪያ ታህሳስ 27/2004 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ፌዴራል

ወደ ገፅ 15 ዞሯል

## በእነውብሸት የይቅርታ ጉዳይ ከማረሚያ ቤት አስተያየት ቀረበ

በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ጥር 17/2004 ዓ.ም. በእስራትና በብር ቅጣት የተቀጡት ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬና አቶ ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር መንግስትን ይቅርታ የጠየቁበት ሂደት ከማረሚያ ቤት አስተያየት ቀርቦበት ሚያዝያ 29/2004 ዓ.ም. ፍትሕ ሚኒስትር መድረሱ ታወቀ፡፡

በፍትሕ ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ማስተባበሪያ ኃላፊ የሆኑት አቶ ደሳለኝ ተሬሳ ለፍትሕ እንደገለፁት ‹‹በፍርደኞቹ ላይ ከማረሚያ ቤት የመጣው አስተያየት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት አማካኝነት ለይቅርታ ቦርድ በሕጉ መሰረት ይቀርባል፡፡›› ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛ ሆና በመገኘቷ 19 ዓመት ፅኑ እስራት የተፈረደባት ወ/ሮ ሂሩት ክፍሌ ከውብሸትና ከዘሪሁን በፊት መንግስትን ለጠየቀችው ይቅርታ ከማረሚያ ቤቱ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

በሰሜን ጉንደር ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ከሁለት ሺህ በላይ ገበሬዎች ከእርሻ መሬቶቻቸው ተፈናቅሉ ተባለ 15

ከመላው ዓለም የተመረጡ አርቲስቶች በለንደን ኦሎምፒክ ፌስቲቫል ላይ እንዲገኙ ተጋበዙ
-ከኢትዮጵያ በዕውቀቱ ሥዩም ተጋብዟል 15

ኢቲቪ በ<<አኬልዳማ>> ዘገባው መቀጣት ይገባዋል ተባለ 15

በተመሳሳይ ክስ እና በአንድ ችሎት የተለያዩ ሁለት ውሳኔዎች የተሰጡበት የተመሰገን የፍርድ ቤት ውጣ ውረድ 10

ወጣቷ ህይወቷ አልፎ ገደል ውስጥ ተጥላ እና በአውሬ ተበልታ ተገኘች 15

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅትና በአሳታሚዎች መካከል ዛሬ ውይይት ይደረጋል 15

አንድነት የስነ ጥበብ ባለሙያዎች የሚመሩት የውይይት መድረክ አዘጋጀ 15

ፕ/ት ኦባማ ነፃ ፕሬስ በምግብ ራስን ለመቻል የሚኖረውን ሚና አጉልተው እንዲሚገቱ ተጠየቀ 15

# የኢትዮጵያ ነዳጅ ማግኘት ግጭቶችን ይቀሰቅሳል?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በቀደመው ሳምንት በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የአለም የኢኮኖሚ ፎረም ላይ ለመሳተፍ ከመጡና ከፎረሙ በፊት በተካሄደው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ፎረም ላይ ለተሳተፉ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች እና የሀገር ውስጥ ድርጅቶች አቶ መለስ አንድ ከባድ ዜና ይዘው ቀረቡ። በዚህ ዓመት መጨረሻ አልያም በሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ኢትዮጵያ የመጨረሻውን የነዳጅ ፍለጋዋን እንደምታጠናቅቅ ተናገሩ። የእርሳቸው ግምት ዕውን መሆን ከቻለ ሀገሪቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ነዳጅ ላኪ ሀገርነት ትቀየራለች። የዚህ የተፈጥሮ ሀብት መገኘትም የኢትዮጵያን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በመሰረታዊነት ይቀይረዋል። ኢትዮጵያን መሰል ሌሎች የሽግግር ማህበረሰቦች የተፈጥሮ ሀብቱን ማግኘታቸውን ተከትሎ ያጋጠሟቸው ሀገራዊ ውጥንቅጦች የርሷም ዕድል ላለመሆናቸው የሚያስረግጡ ነባራዊ ሀቆች ያሉ አይመስልም። በዚህ ጉዳይ ላይ የሚፅፉ አጥኚዎች የነዳጅን መገኘት ተከትለው የሚከሰቱትን ሁነቶችን "the three R's" (Renter states, Rent-seeking and Repression) ብለው ይጠሯቸዋል። እንደ መምህራኑ ክርክር አስቀድመው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓትን ገንብተው ያልጨረሱ ሀገራት ይህን የተፈጥሮ ሀብት ማግኘታቸው ሀገራዊ አደጋዎችን ያስከትልባቸዋል። ጥቂት ገዢ የፖለቲካ ልሂቃን ሀብት የሚሰበስቡበት፣ የእርስ በእርስ ግጭቶች የሚበዙበት፣ የጥቅመኝነት ፖለቲካ የሚጎለብትበት ከባረኮትነት ይልቅ በመርገምትነት እንዲሰየም አድርጓል። እነዚህን ተያያዥ ሀገራዊ አደጋዎች ለማርገብ በመፍትሔነት የሚቀርበው የነፃ ተቋማት ህልው መሆን እና የፖለቲካዊው ስርዓት ዴሞክራሲያዊነት ቢሆንም ኢትዮጵያ ሁለቱንም ሁነቶች ልትከውናቸው አለመቻሏ አደጋዎቹን ይበልጥ ነባራዊ ያደርጋቸዋል። ከጥቂት ዓመታት በፊት የወጣው የጋሉፕ ጥናት ኢትዮጵያውያን ተቋሞቻቸው ላይ ያላቸው እምነት ከሰሀራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ዜጎች አቻዎቻቸው እጅግ ያነሰ መሆኑ፣ ስርዓቱ ‹‹እየከሰሙ ካሉ›› መንግስታት ተርታ መሰለፉ፣ የመሬት ወረራውን ተከትሎ በጋምቤላ የተከሰተው የታጣቂዎች ጥቃትም ሆነ የክልሉ ነዋሪዎች የከረረ ተቃውሞ አልፎም የኦጋዴን ሰላም አልባነት፤ ኢትዮጵያ የቤት ስራዋን አስቀድማ ስላለመስራቷ የሚመሰክሩ ይመስላሉ።

## ሰላም አልባ ሀገር?

ብዙዎቹ ደሃ ሀገራት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ለመጠቀም በሚሞክሩባቸው ጊዜያት ለተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት መሠረታዊ ናቸው የሚባሉትን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ካለመገንባታቸው በተነሳ ወደ ከፋ የእርስ በእርስ ግጭቶች ሲገቡ ተስተውሏል። በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና በእርስ-በርስ ግጭቶች መሀከል ያለውን ተዛምዶ በመፈተሽ የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲው የነገረ-ሀብት አጥኚ ፖል ኮሊየር እና አንኪ ሆፍለር ቀዳሚ ናቸው። "Greed and grievance in civil war" እና "On the civil war in Africa" በሚሉ ርዕሶች ያሳተሟቸው ጥናቶች በተለይ በነዳጅ ሀብት አጠቃቀም እና ይህንን ተከትለው በሚከሰቱ ግጭቶች መብዛት መሀከል ያሉትን ነባራዊ ሁነቶች በጥብቅ ኀልዮታዊ መደላድል ላይ የተደገፉ ሙግቶችን አካተው ያተቱባቸው ስራዎቻቸው ናቸው። እ.ኤ.አ. ከ1960 እስከ 1999 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት በ161 አገራት የተከሰቱትን 78 የእርስ በርስ ግጭቶች በማጥናት እንደሚደመድሙት ከሆነ በተለይ ከአንድ ሀገር ቀዳሚ ምርት /Primary commodity/ የሚገኝ የኤክስፖርት መጠን ከአጠቃላይ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት /GDP/ ከፍተኛውን ድርሻ መያዝ ሲጀምር ሀገሪቱ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት የምትገባበት ዕድል እንዲሁ እየጨመረ ይሄዳል። እንደ እነ ኮሊየር መላምት ይህ የተፈጥሮ ሀብት የኤክስፖርት ድርሻ ከዜሮ ወደ 32% ቢያድግ፣ የግጭቶቹ የመነሳት እድልም እንዲሁ በ22% ይጨምር። "On the incidence of civil war in Africa" በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ከሆኑት መካከል አንደኛው እና ዋነኛ የሆነውን ነዳጅን በመውሰድ፤ በደረሱበት ድምዳሜ የነዳጅ ሀብት የሀገር የኢኮኖሚ መሰረት መሆኑ፣ መገንጠልን ግባቸው የሚያደርጉ ጦርነቶችን እንደሚቀሰቅስ ይከራከራሉ። ፀሐፊዎቹ ‹‹ሁሉን የራስ ለማድረግ የመፈለግ›› /greed thesis/ ብለው የጠሩትን ሀቲት እንደሚያብራሩት ከኢኮኖሚያዊ የገቢ ኢ-እኩልነት፣ ከብሄር ጥያቄ አልያም ከዴሞክራሲ ዕጦት ይልቅ የነዳጁ በአንድ አካባቢ መገኘት የመገንጠል ሀሳብ አቀንቃኞችን ጦርነቱን ለመቀስቀስ የተሻለ ትርፍ እንደሚያገኙ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል። ጆናታን ዲያ ጆን የተባሉ ተመራማሪ በበኩላቸው " oil abundance and violent political conflict: A critical assessment" በሚለው ፅሁፋቸው የነዳጅ ሀብት የሚገኝበት ቦታ የቀደመ ዘውግ-ተኮር እንቅስቃሴ ያቆጠቆጠበት አካባቢ ከሆነ የአማፂዎቹን እንቅስቃሴ እጅግ ደም አፋሳሽ ያደርገዋል። የብሄር ቅራኔው መነሻ ‹በአካባቢያችን ባለው የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ አልተጠቀምንም› ከሚል ቅሬታ ከመወለዱ በተጨማሪ እነ ኮሊየር እንደሚጠቅሱት አማፂዎቹ የጦርነቱን ጉዳትና ጥቅም ሲያሰሉ በተለይ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ወደ ሁለተኛው የስሌት ድምዳሜ ማድላታቸው ግጭቱን እጅግ መራራ እንዲሆን ያደርገዋል። በዚህ ጭብጥ ላይ የፃፉት የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲው መምህር ማካርታን ሃምፍሬይስ "Economics and violent conflict" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው የነዳጁ በአንድ የተወሰነ አካባቢ እና ግዙፍ ቅሬታ የነበረባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ባሉበት የሚገኝ ከሆነ የቡድኑ አባላት አካባቢያቸውን ከማዕከላዊ መንግስቱ ቢገነጥሉ የተሻለች ‹‹ሀገር›› እንደምትኖራቸው እንዲያምኑ ይገፏቸዋል። ይህም ለመገንጠል የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች በጠንካራ መሰረት ላይ ያቆምላቸዋል።

ይህን የሀገር ሰላም-አልባነት የሚያባብሰው ሌላኛው ምክንያት ነዳጅ (የሀገሪቱ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከመሆኑ አንፃር) በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖረውን የዋጋ አለመረጋጋት ተከትሎ የሚፈጠረው የመንግስታቱ ምርጫ የለሽ እርምጃ ነው። የነዳጅ በአለም አቀፉ ገበያ ላይ ያለው ዋጋ እየዘቀዘቀ ሲመጣ ከነዳጁ የሚገኘውን ሀብት ተማምነው በማህበረሰቡ ላይ አነስተኛ ታክስ ጥለው የነበሩት ገዢ ፓርቲዎች፤ የዋጋውን ማሽቆልቆል ተከትሎ የሚፈጠረውን ሀገራዊ የገቢ ክፍተት ለመሙላት ከዚህ ቀደም ያላስተዋሏቸውን የሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች ያስሳሉ። በታክስ አሰባሰብና አስተዳደር ላይ የነበራቸው ተቋማዊ እና ቢሮክራሲያዊ አቅም በነዳጅ ገቢ ምክንያት የላላ የነበረ መሆኑ መንግስታቱን ከማህበረሰቡ የሚፈልጉትን ገቢ በጉልበት ወደ መሰብሰብ ይገፉቸዋል። የጉዳዩ አጥኚዎች ይህን የመንግስታቱን አካሄድ ‹‹በላዔ-ሰብ መንግስትነት›› (Predatory state) ሲሉ ይጠሩታል። ይኸኛው የገቢ አሰባሰብ አማራጭም በስርዓቱ እና በማህበረሰቡ መሀከል ያለውን ተለምዷዊ ቁርኝት በማላላት እና አመፀኝነትን በማስፋፋት የተገንጣይ ንቅናቄዎችን የሞራል እና የድጋፍ መሰረት ያጠናክራል።

የነገሩ ተከታታዮች በተጨማሪ የሚጠቅሱት ግጭት-አባባሽ ምክንያት በኒጀር ዴልታ ነዋሪዎች እና በናይጄሪያ ማዕከላዊ መንግስት መካከል የተፈጠረውን ግጭት እንደ አብነት በመውሰድ ነው። ይህን ግጭት ምሳሌ የሚያደርጉት ‹‹ከነዳጅ ማውጣት ጋር የሚያያይዘውን የስነ-ምህዳር መዛባት መከራከሪያነት በመጥቀስ ነው። በዚህ መከራከሪያ መሰረት የአፍሪካ ሀገራት ጠንካራ መሰረት ያለው የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ አለመገንባታቸው ነዳጅ ይኖርባቸዋል የሚባሉትን ቦታዎች ለድንበር-ዘለል ኩባንያዎች እንዲለቁ ይገደዳሉ። ካምፓኒዎቹ ነዳጁን ለማውጣት በሚያደርጉት ጥረት በአካባቢው ያለውን የሥነ-ምህዳር መዛባት ጨምሮ ሌሎች የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብቶች ጠቃሚነት የሚያቃውሱ እርምጃዎች ይወስዳሉ። ለዚህ መሰል ጉዳቶች የአካባቢው ነዋሪዎች ቀዬያቸውን ትተው እንዲሸሹ ከመደረጋቸው በተጨማሪ ተገቢ የማካካሻ ክፍያ ማግኘት አለመቻላቸው በፖለቲካው ስርዓት ላይ የሚኖራቸውን ቅሬታ ያበረታዋል። በኒጀር ዴልታ ጉዳይ ላይ የፃፉት አዴሪጁአየፍሱ እንደሚሉት በአካባቢው ያሉት ነዋሪዎች ጥያቄ ያጠነጠነው በመሬት ባለቤትነት እና የተፈጥሮ ሀብቱን ለመጠቀም በሚል ከይዞታቸው የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ያነሱት የካሳ ጥያቄ እንደሆነ "Oil dependence and civil conflict in Nigeria" በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው ያወሳሉ።

ፕ/ር ፓል ኮልየር እና አንኪ ሆፍለር "Greed and grievance in civil war" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው የሚያነሱት ተያያዥ ማህበረሰባዊ ቀውስ የዜጎችን የተፈጥሮ ኃብት ወደ ተገኘበት አቅጣጫ መፉለስን ያባብሰዋል የሚል ነው። ከኢኮኖሚያዊ መላሽቅ የሚነሳው ቅጥ ያጣ ስራ አጥነት መለያቸው በነበረው ደሀ ሀገራት የተፈጥሮ ሀብቱ መገኘት የሀገራቱን የሰራተኛ ሀይል ነዳጁ ወደተገኘበት አካባቢ በብዛት እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል። የኢትዮጵያ ቋንቋ ተኮር ፌዴራሊዝም የዜጎችን የመንቀሳቀስ መብት ስለመገደቡ ብዙ አጥኚዎች እንደመስማማታቸው፤ ይህ ዓይነት የሌላ ብሄር ተወላጆች ‹‹ወደ ማይመለከታቸው›› ክልል ለመሄድ መሞከር ባለፉት ሃያ ዓመታት ከተከሰቱት የብሄር ግጭቶች አንፃር አደጋን ሊያመጣ ስለመቻሉ አንዳንድ የነገሩ ታዛቢዎች ይጠቅሳሉ። በቅርቡ ‹‹ወደ ሀገራችሁ ግቡ›› በሚል የተከሰተው የጉራፈርዳ ነዋሪዎች መፈናቀል አልፎም የ1994ቱ የጋምቤላ ‹‹ከሀገራችን ውጡ›› መሰል ግጭቶች አንፃር፤ ከሁለቱ ክልሎች ውጪ ያሉ ነዋሪዎች ነዳጁ ይገኝባቸዋል ወደተባሉት የጋምቤላ እና የኦጋዴን ክልሎች መሄድ ብሄር-ተኮር መተናነቆችን ሊያባብስ የሚችልበትን ዕድል የሚያሰፋ ይመስላል።

በነዳጅ መገኘት እና በማህበረሰባዊ አለመረጋጋት ላይ የፃፉ ምሁራን እንደሚደመድሙት ከሆነ ከላይ የተጠቀሱትን ግጭቶች ለማርገብ ማዕከላዊ መንግስቱ አቅም አልባ የሚሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያውን ሀሳብ የሚያብራሩት ፕ/ር ጆናተን ዲያ ጆን እንደሚሉት ስርዓቱ ከነዳጁ በሚገኝ ሀብት በመተማመኑ ብቻ ጠንካራ ተቋማት አለመገንባቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ቅሬታዎችን ለመረዳት የሚያስችል ስርዓት አይኖረውም። በዚህም ምክንያት የተገንጣይ እንቅስቃሴ አራማጆች ጉዳዩን ወደ አደባባይ እስኪያወጡት ድረስ ስርዓቱ በዝንጋኤ የተዋጠ ይሆናል። ሚካኤል ሮስ የተባሉ አጥኚ በበኩላቸው ማዕከላዊ መንግስቱ ዘግይቶም ቢሆን ግጭቱን ለማርገብ የሚመርጠው መንገድ ወታደራዊ አፈናን መሆኑን ይናገራሉ። "oil and democracy revisited" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት ፕ/ር ሮስ እንደሚከራከሩት ከነዳጅ ከሚገኘው ሀብት ብዙውን ለወታደራዊ አቅሙ ማጎልበቻነት መጠቀሙ በቂ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ካለመገንባቱ ጋር መዛመዱ፣ ግጭቶቹን በመሳሪያ ሀይል ለመፍታት መግፋቱ፤ በውጤቱም የግጭቱን መነሻ ሥረ-ምክንያት ማባባሱ ገዢውን የፖለቲካ ቡድን ፖለቲካዊ ቅቡልነትና አቅም-አልባነት የሚያስረግጥ ሁለተኛው ተጠቃሽ ምክንያት ነው።

## የዴሞክራሲ ቁልቁለት

ከነዳጅ የሚገኝ ገቢ የሀገሪቱ ዋነኛ የገቢ ምንጭ መሆን ሲጀመር የፖለቲካው ስርዓት ዲሞክራሲያዊነት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶች ‹‹ዴሞክራሲ እና የነዳጅ ሀብት ተጣሮሻዊ ዝምድና አላቸው›› ወደሚል ጠንካራ ድምዳሜ ያዘነብላሉ። የየል ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪ ተድ ዱኒንግ "Crude democracy: natural resource wealth and political regimes" በሚለው ተጠቃሽ ጥናታዊ ስራቸው የነዳጅ ሀብት በደሀ ሀገራት መገኘት አምባገነንነትን ከማፋፋት በዘለለ አንዳችም ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መስፋፋት የሚያደርገው አስተዋፅኦ እንደሌለው ያወሳሉ። በነዳጅ ላይ ሀገራዊ የኢኮኖሚ መሰረታቸውን ያዳበሩ አገራት የሚተገብሩትን ፖለቲካዊ ስርዓት ‹‹የነዳጅ ዴሞክራሲ›› /crude democracy/ ሲሉ የሚጠሩት ፕ/ር ታድ ዱኒንግ፤ ‹‹የነዳጅ ዋጋ ሲንር፣ ሰዋዊ ነፃነት ቁልቁል ይንሸራተታል›› የሚለው ሚልተን ፍሬድማን መላምት ኃልዮታዊም ሆነ ተጨባጭ ሙግቶች ላይ መቆሙን ይናገራሉ። ይህን የሙግት ድልዳል ፅንሰ ሀሳባዊ መከራከሪያ በመስጠት የመጀመሪያው መሆናቸው የሚጠቅስላቸው ፕ/ር ሚካኤል ሮስ እ.ኤ.አ. በ2001 ዓ.ም. ‹‹Does oil hinder democracy?" በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ስራ ነዳጅ-መር የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ባላቸው ሀገራት ለሚስተዋለው አምባገነናዊ ስርዓት መጠናከር የኪራይ ሰብሳቢ መንግስት ሀቲትን በመሰረታዊ መሞገቻነት አቅርበዋል።

የአንድ ሀገር የነዳጅ ድርሻ ከአጠቃላዩ ሀገራዊ ገቢ አንፃር እየጨመረ ሲመጣ የመንግስታዊ ስርዓቱን ሚና ወደ ሀብት አከፋፋይነት ይቀይረዋል። ማዕከላዊ መንግስቱ ይህን ሀብት በተመለከተ የሚኖረው ሚና ስርዓቱን ወደ ኪራይ ሰብሳቢ መንግስትነት እንደሚቀይረው የሀሳቡ ተንታኞች ይናገራሉ። የገዢነት ዕድል የሚያገኘው የልሂቃን ስብስብ ከነዳጅ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በቀዳሚነት ለፖለቲካዊ ድጋፍ ማሰባሰቢያነት ይጠቀምበታል። ቤንጃሚን ስሚዝ "Oil wealth and regime survival in the developing word" በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚያትቱት ሀብት የማከፋፈሉን ስራ የሚከውነው ገዢ ፓርቲ ሀገራዊውን የነዳጅ ሽያጭ ገቢ በተቀናቃኝነት የቆሙትን ዜጎችንም ሆነ ተቋማት ድጋፍ ለመግዛት ያውለዋል። ይህን ፖለቲካዊ ሙስና ለማጋለጥ የተሻለ አቅም ሊኖራቸው ይችል የነበሩት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በዚህ የጥቅመኝነት ፖለቲካ ውስጥ ይወድቃሉ። ፕ/ር ሮስ ለዚህ በማሳያነት የሚጠቅሱት የአንጎላውን ፕሬዚዳንት ዶስ ሳንቶስ አካሄድ ነው። ፕ/ት ዶስ ሳንቶስ ሀገራቸው ከነዳጅ ያገኘችውን ገቢ በመጠቀም በስማቸው ባቋቋሙት የበጎ አድራጎት ድርጅት በኩል የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የሲቪል ማህበረሰቡን መንቀሳቀሻ ክበብ አጥብበውታል። ብዙ የሀገሪቱ ተመራማሪዎችን እና ተቀናቃኞችን በገንዘብ በመደለል ብዙም ፋይዳ በሌላቸው ኮንፈረንሶችና ፕሮጀክቶች በመጥመድ የተፈጥሮ ሀብቱን ለአምባጋነናዊ ስርዓታቸው መጎልበት መጠቀማቸው የሌሎችም አፍሪካውያን የተለመደ አካሄድ እንደሆነ ሚካኤል ሮስ ያወሳሉ። ቤንጂማን ስሚዝ በበኩላቸው ይህ ዓይነቱ አካሄድ በሁለት አውዶች ላይ እንደሚንተራስ ይናገራሉ። የመጀመሪያው የነዳጅ ዋጋ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ያለው ዋጋ ከፍ እያለ ሲመጣ መንግስታቱ የጥቅመኝነት ትስስሩን ይበልጥ ማጠናከር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ይህን ማድረጋቸው ፖለቲካዊ ስርዓቱን ከመወከል ባለፈ ኢኮኖሚው ውስጥ በብዛት የሚያፈሱት ገንዘብ ሀገሪቱን በዋጋ ንረት እንድትናጥ ሲያደርጋት፤ በተፃራሪው በሁለተኝነት የሚጠቀሰው የነዳጅ ዋጋ ማሽቆልቆል ስርዓቱ በተለምዶው መንገዱ መሄድ እንዳይችል ስለሚያደርገው መንግስታዊ አቅሙን ይፈትነዋል።

እነ ሚካኤል ሮስ ‹‹ፖለቲካዊ የደች ልክፍት›› /Political dutch disease/ ብለው የሰየሙት ተጠያቂነት የሌለበት ፖለቲካዊ ስርዓት ሌላኛው የነዳጅ ላኪ ሀገራት ዴሞክራሲያዊ መንሸራተትን የሚያብራራ ሀሳብ ነው። እንደ ፀሐፊዎቹ መከራከሪያ እኒህን መሰል ሀገራት ብዙውን ሀገራዊ ወጪያቸውን ከነዳጅ ገቢ ስለሚያገኙ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰበው ታክስ እጅግ አነስተኛ ይሆናል። የሚሰበሰበው ታክስ አነስተኛ መሆን ለማህበረሰቡ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ አቅም መስጠቱ ዜጎች ዴሞራክሲ-ተኮር ለሆኑ እንቅስቃሴዎች የሚኖራቸውን መነሳሳት አነስተኛ ያደርገዋል። "A critical analysis of the role of oil in hindering transition towards democracy in the middle east" በሚለው ፅሁፋቸው አሳድ አህመድ የተባሉ ፀሐፊ ይህ አነስተኛ ሊባል የሚችል የታክስ መጠን መኖር ፖለቲካዊ ስርዓቱ ከፖለቲካው ማህበረሰብ ሊኖረው የሚገባውን የተጠያቂነት ባህርይ ይገድለዋል። በዚህ መልክ የሚደራጀውን የመንግስትና ህዝብ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ ተዛምዶ ለመግራት ወደ አደባባይ የሚመጡ የፖለቲካ ስብስቦችም ካለ ዕጣ-ፈንታቸው በስርዓቱ ወታደራዊ ጡንቻ መደፍጠጥ ይሆናል። ፕ/ር ሮስ እንደሚጠቅሱት ስርዓቱ ብዙውን ከነዳጅ የሚገኝ የገቢ መጠን ለወታደራዊ እና ደህንነት ተቋም ግንባታ ማዋሉ፤ ማህበረሰባዊ ተጠያቂነትን ከማላላቱ ጋር ተዳምሮ፣ መንግስታዊ ስልጣኑን መልቀቅ፦ የተገኙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችንም አሳልፎ መስጠት ከመሆኑ በመነሳት ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመሞከር ገፊ ምክንያት በማጣቱ ስልጣኑን ለመጠበቅ መራር እርምጃዎችን ይወስዳል። እነዚህን ከነዳጅ እና ከዴሞክራሲ ጋር የተዛመዱ ሁኔታዎችን ከመንግስታት በስልጣን የመሰንበት ዘመን ጋር አጣምረው ያጠኑት ቤንጃሚን ስሚዝ፤ ገዢ ፓርቲዎቹ የተጠቀሱትን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች (ታክስን መቀነስና ጥቅመኝነትን ማስፋፋት) ሲወስዱ አስቀድመው የማይጠየቁበትን ስርዓት በማበጀታቸው ረዥም ዘመናትን በስልጣን ለመቆየት ይቻላቸዋል። ‹‹በዚህም ምክንያት›› ይላሉ ፕ/ር ሚካኤል ሮስ የቀደመ መላ-ምታቸውን በተሻለ ባብራሩበት "Oil democracy revisited" በሚለው ፅሁፋቸው ‹‹መንግስታት፦ ዜጎች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚኖራቸውን መነቃቃት ይገድሉታል።››


የነዳጅ ሀብትን በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ለሀገራዊ ክስረት የሚዳረጉ መንግስታትን ‹‹የተረገሙ ሀገራት›› /Cursed state/ ብለው የሚጠሩ ፀሐፊዎች የእነዚህ ሀገራት አንዱ መሰረታዊ መለዮ አድርገው የሚያነሱት የተቋማትን መድቀቅ ጉዳይ ነው። የተፈጥሮ ሀብቱ መኖር ከሀገሪቱ የድህነት ጥልቀት እና የግጭቶች መብዛት ጋር ላለው ግርንቢጣዊ ግንኙነት በምክንያትነት የሚጠቀሰው ሁነት፤ ገዢ የፖለቲካ ልሂቃኑ ከሚከተሉት የተበላሸ ፖሊሲ የተነሳ ሀገራዊ ተቋማቱ በሚፈለግባቸው አቅም የዳበሩ አለመሆናቸው ነው። ጄፍሪ ሳክ እና ዋርነር "The Big push, natural resource booms and growth" ፅሁፋቸው ላይ ይህን ጉዳይ ያነሳሉ። ተቋማዊ ተጠያቂነትን ያዳበሩ እና ከፖለቲካዊ ታማኝነት ይልቅ በክሂላቸው በተመረጡ ዜጎች የሚመሩ አገራት የነዳጅ ገቢን ኢ-ፍትሃዊ ክፍፍልን ስለሚያስቀሩ ለማህበረሰባዊ ብልፅግና የተሻለ አበርክቶት ይኖራቸዋል። እነጄፍሪ ሳክ እንደሚያወሱት እንዲህ ዓይነት ተቋማት የኪራይ ሰብሳቢ መንግስት ዋነኛ መለዮ የሆነውን የሙስና መፋፋት ስለሚገድቡ የተፈጥሮ ሀብቱን ወደ መርገምትነት የመቀየር ዕድል ያጠባሉ። በተቋማት የጥራት ደረጃ ነዳጅ፤ ላኪ የሆኑ ሀገራትን በማወዳደር ሁለቱ አጥኚዎች እንደሚደመድሙት ከቦትስዋና እስከ ማሌዥያ ያሉት የተሻለ ፖለቲካዊ መረጋጋት ሲኖራቸው፤ ከአልጄሪያ እስከ ዛምቢያ በሌላ ጫፍ ተቋማዊ ነፃነትንም ሆነ ተጠያቂነትን ባለማዳበራቸው የነዳጅ ሀብቱ ለሚቀሰቅሳቸው ግጭቶች ተጋልጠዋል።

## ነዳጅ ለኢኮኖሚ እድገት?

በኢትዮጵያ በሚቀጥለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይገኛል የተባለው ነዳጅ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያፋጥነው እንደሚችል በቁፋሮው ላይ የተሰማሩትም ድርጅቶች ሆኑ አቶ መለስ ደጋግመው ተናግረዋል። አምባገነናዊ ስርዓት ባሰፈኑ የአፍሪካ ሀገራት ላይ ጥናት ያደረጉ ፀሐፊዎች ይህ የሰዎቹ መላምት ዕውን ስለመሆኑ ይጠራጠራሉ።

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# ተቀናቃኝ ቡድኖችና ፖለቲካ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ተመስገን ደሳለኝ በተቀናቃኝ ቡድኖች ላይ አዲስ የመነጋገሪያ ርእስ ከፍቶአል (ግንቦት 3፣ 2004)፤ ጉዳዩ በጣም አንገብጋቢና በጣም ወቅታዊ ነው፤ እንደተለመደው አንብበን ችላ የምንለው ጉዳይ አይደለም፤ ሁላችንም በተቻለን መጠን እውነትን ይዘን ያለ ይሉኝታና ያለፍርሃት በራሳችን ላይ እንዝመትና እውነትን ይዘን እንነሣ።

በ1997 መኢአድ፣ ኢዴፓ፣ ኢዴሊና ቀስተ ደመና የሚባሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ሆነው ቅንጅትን ፈጠሩ፤ ነገር ግን የመኢአድን ከአቶ ኃይሉ ሻውል፣ ኢዴፓን ከአቶ ልደቱ ህልውና ለመለየት በፍፁም የማይቻል ሆነ፤ ስለዚህም የቅንጅትን ህልውና ፈተና ውስጥ ከተቱትና ተበታተነ፤ እስካሁን ድረስ ህልውናውን ከሕዝብ ህልውና ጋር አስተሳስሮ የቆየ የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም፤ በገዢው ወንበር ላይ በጠመንጃ ኃይል ከወጡ በኋላ ጉልበትና ሀብት ሁሉም በጄ ሁሉም በደጄ ብለው ኢሰፓና ወያኔ/ኢሕአዴግ ሎሌዎቻቸውን ሰብስበው ፓርቲ ቢሉ ዋጋ እንደሌለው አይተናል፤ ደርግ በጉልበት ስልጣን በመያዙና ስልጣንን ጉልበት ብቻ በማድረጉ እንደተጠላ ተፍረክርኮ አይዞህ የሚለው ሳያገኝ ወድቆ ተበታተነ፤ ወያኔ/ኢሕአዴግ እንደገና በጉልበት ኢሰፓን ተካ፤ ሥልጣንን ጉልበት ብቻ አድርጎም እየገዛ ነው፤ በኢሰፓ ዘመን ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች በስምም በተግባርም አልነበሩም፤ በወያኔ/ኢህአዴግ ዘመን የፖለቲካ ፓርቲዎች በስም ተፈልፍለው በተግባር ተለጉመው በመኖና ባለመኖር መሀከል እያጣጣሩ አሉ፤ ያውም ምርጫ ቦርድ መልካም ፈቃዱ ሲሆን!

ለይስሙላ የተቋቋሙት ፓርቲዎች በምርጫ ጊዜ ትንሽ የተፈቀደላቸውን ያህል አባላት አስመርጠው በብሔራዊ ምክር ቤት (ፓርላማ) ያስቀምጣሉ፤ የተከበሩት አባላትም ቤትና ደመወዝ ያገኛሉ፤ የመጨረሻው ዓላማቸውም ይኸው ነው፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች በስም ተሰይመው፣ ህልውናቸውን በአንድ ወይ በሁለት ሰዎች ስም ያስከብራሉ።

በወያኔ/ኢሕአዴግ ዘመን አንድ የተለመደ አጉል ፈሊጥ አለ፤ በሆነ ባልሆነው ወያኔ/ኢሕአዴግን መውቀር ያስመሰግናል፤ በአንጻሩ በተቀናቃኝ ቡድኖች ወይ በመሪዎቻቸው ላይ ትችት ማቅረብ እንደክህደትና ከኢትዮጵያዊነት መስመር እንደመውጣት ይታያል፤ ይህ በተደጋጋሚ የታየ ነው፤ በቅንጅት መሪዎች መሀከል የነበረውን የስልጣን ሽኩቻ በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ስናገር በመጀመሪያ የራዲዮው ጠያቂ የነበረችው አነጋገሬን አልወደደችውም፤ የግል ስሜትዋን ለመግለጽ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደገና ደውላ ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ጠየቀችኝ፤ ወሬው ከተላለፈ በኋላም ብዙ ሰዎች እየደወሉ ለብቻቸው ብታነጋግራቸውና ብትመክራቸው ይሻል ነበር በማለት የወቀሳ ትችት አቀረቡልኝ፤ እነዚህ ሰዎች የማከብራቸውና ሀሳባቸውን የማልንቅባቸው ናቸው፤ ለሁሉም የመለስሁላቸው እነሱ ለእኔ የሰነዘሩትን ምክር አንደኛ እኛ ሳናስብበትና ተግባራዊ ሳናደርገው ቀረን ብለው መገመታቸው የሚያሳዝን መሆኑን ነበር፤ ሁለተኛ ሁለትና ሶስት ወራት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ በተዋናውያኑ በራሳቸው እውነቱ ገሀድ እንደሚወጣ ነግሬአቸው ነበር፤ እኔ የሥልጣን ጥሙን ሽኩቻ በማንሣቴ ለጠብ በር የከፈትሁ የመሰላቸው ሰዎች በቅንጅት ውስጥ የነበረውን ትግል የማያውቁ ናቸው፣ ገና ቀደም ብዬ ሌላው ሁሉ ካቃተኝ በኋላ የስልጣን ሽኩቻው ቅንጅትን እየጎዳው እንደሆነ ስለተረዳሁ ለቅንጅት ሊቀ መንበር ለኃይሉ ሻውል ደብዳቤ ጽፌ ከምክር ቤት መሰናበቴን አሳወቅሁ፤ ከቅንጅት ምክር ቤት ስወጣ በይፋ በአደባባይ ሳልናገር መቅረቴ ስሕተት ነው፤ መናገር ነበረብኝ፤ ግን ያው በኋላ ከብዙ ሰዎች የሰማሁት ወቀሳ በእኔም ውስጥ ስለነበረ ይሉኝታ ይዞኝ ተሳሳትሁ፤ ከቃሊቲ ከወጣን በኋላ በህንድ አገር ሀኪም ቤት ማጅራቴን በመጋዝ ለመተርተር ስዘጋጅ ድንገት ሳልነቃ ብቀር እውነት ተዳፍኖ እንዳይቀር በማለት ምስክርነቴን ሰጠሁ፤ በዚያን ጊዜ እኔ የነበርሁበትን ሁኔታ በትንሹም ቢሆን ለመገመት ከተቻለ ለእውነት በእውነት ከመመስከር ሌላ ዓላማ እንደማይኖረኝ ለመረዳት እንዴት እንዳስቸገረ እስከዛሬ አልገባኝም፤ ጥርጣሬያችንና አለመተማመናችን ድንበር የለውም ማለት ነው።

ከዚያ በኋላ ብዙ መጽሐፎች ተጽፈዋል፤ ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ፣ ልደቱ አያሌው፣ ደበበ እሸቱ፣ አንተነህ ሙሉጌታ (የመጽሐፉን ርእስ አበላሽቶት ብዙ ሰዎች አላነበቡትም እንጂ በጣም ጥሩ መጽሐፍ) መስፍን ወልደማርያምም ጽፈዋል፤ አሁን ደግሞ ሲሳይ አጌና (ከውጭ እንደጋዜጠኛ ይሁን ወይስ የውስጥ መስሎ አላውቅም፤ ነገር ግን በራድዮ ሲናገር እንደሰማሁት ብርሃኑ ነጋን ከእውነቱ ሊያርቀው በጣም ሲሞክር እውነቱን ይደፈጥጣል)፤ ለማናቸውም ታዛቢዎች ተናገሩት አልተናገሩት በኃይሉ ሻውል፣ በብርሃኑና በልደቱ መሀከል የነበረውን ግልጽ የሆነ ሥርዓት ያጣ ፉክክር ማንም ሊክደው ወይም ሊያድበሰብሰውና ሊያልፈው አይችልም፤ ለምን ቅንጅት ፈራረሰ? አንዳንዶቻችን ክብራችንን አንጥፈን ለማስታረቅ ሞክረናል፤ አንድ ምሳሌ ለመስጠት በቀጠሮ ሄደን አቶ ገብረጻድቅ፣ አቶ ይልማ ይፍሩና እኔ ከአቶ ኃይሉ ሻውል አጥር ውጭ ለእኩል ሰዓት ያህል መኪና ውስጥ ቆይተን ሳይሆንልን ተመልሰናል፤ በኋላም አሜሪካ ሆኖ በነጭ ወረቀት ከሕግ ውጭ የሆነ የሹም-ሽር ሲያደርግ ሀሳቡን ለማስለወጥ አሜሪካ ስልክ ደውዬ ለማነጋገር ብሞክር እኔንም ባላንጣው አደረገኝ፤ ተፎካካሪዎቹን ለማቀራረብ፣ ለማስታረቅና ወደአብሮ መሰለፍ ለማምጣት በተደረገው ጥረት የተሳተፉትን ሁሉ ተፎካካሪዎቹ በጥላቻ ይመለከቱአቸው ጀመሩ።

በልደቱ የተጀመረው የቅንጅት መገነጣጠል፣ በብርሃኑ ነጋና በኃይሉ ሻውል ቀጥሎ ብርቱካን የምትመራው አንድነት ብቻውን ቀረ፤ በአንድነትም ውስጥ ገና ከመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ ጀምሮ ብርቱካን በመመረጥዋ ቅር ያላቸው አባሎች አኩርፈው ችግር ተፈጥሮ ነበር፤ ብርቱካን ስትታሰር ኤንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በጉጉት ሲጠብቀው የነበረውን ወንበር አገኘና የአምባገነንነት አገዛዙን በግምባር ቀደምትነት ከዶር. ኃይሉ አርአያና ከአቶ ዓሥራት ጣሴ ጋር ጀመረ፤ ሁሉም ቢያንስ ከሁለት ሺህ ብር በላይ የወር ደመወዝ ያገኙ ነበር፤ እንዲሁም የጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ሁሉ በጥሩ ደመወዝ ተሰንገው የተያዙ ነበሩ፤ እነዚህ ናቸው ሎሌዎች አይደለንም የሚሉት፤ ከበስተጀርባቸውም የብሔራዊ ምክር ቤት ገብተው ሌሎቹ ቃሊቲ በነበሩበት ጊዜ ደመወዝ ሲበሉ የነበሩ ናቸው፤ ያንን የደመወዝ ወንበር እንደያዙ ለመቀጠል የተመኙ የአንድነት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የምክር ቤት አባላት ነበሩ፤ ግዛቸው እነዚህን ሁሉ ሎሌዎች አሰልፎ ስሙ ወደምግባሩ መራውና የማይበገር አንባ-ገነን ሆነ፤ ከመጀመሪያዎቹ አወዛጋቢ ጉዳዮች መሀከል አባላት በጽሕፈት ቤቱ አዳራሽ ያለፈቃድ እንዳይሰበሰቡ፣ ግዛቸው፣ ኃይሉ አርአያና ዓሥራት ባልፈቀዱት ጉዳይ መወያየት መከልከሉን፣ በነፃነት አባልነታቸውን ለመወጣት የሚፈልጉትንና ከሎሌነት ያፈነገጡትን ሰዎች ለማስወንጀል ማስፈራራት ነበሩ፤ ከውጭም ድጋፍ ነበራቸው፤ የቅንጅት የድጋፍ ኮሚቴ በአሜሪካ ሊቀመንበር ነኝ የሚል አክሎግ ልመንህ የሚባል የማስፈራሪያ ደብዳቤ ጽፎልን እኔ መልስ ሰጥቸውአለሁ፤ ሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮች ዋና ጸሐፊው አቶ ዓሥራት ጣሴ አንደኛ አንዲት ጸሐፊ የነበረች የአንድነት አባልን ያለማስጠንቀቂያና ካሣ፣ ሁለተኛ አንዲት የጽዳት ሠራተኛን እንዲሁም ያለምንም ማስጠንቀቂያና ካሣ ከሥራ ማስወጣቱ ናቸው፤ በነዚህ ምክንያቶች አንድነት ለሁለት ተከፈለ፤ ግዛቸው መርጠው ወንበሩ ላይ ያስቀመጡትን ሰዎች አባርሮ በዶር. ነጋሶ ጊዳዳ፣ በአቶ ስዬ አብርሃና በአቶ ገብሩ ዓሥራት ድጋፍ መሰላሉን ሊወጣ ተመኘ፤ መሰላሉ ወደቀ።

ዛሬ ቅንጅትን ሰባብረው ግልገል የሥልጣን ፈረሶችን የፈጠሩት ሁሉ በሦስት ምክንያቶች ኮስሰዋል፤ አንደኛ ሰውን መግዣ ገንዘብ እያነሰ ነው፤ ሁለተኛ አባሎችም የተሻለ ንቃትና ትምህርት እያገኙ ሎሌነትን እምቢ እያሉ ነው፤ ሦስተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲሶቹን መኳንንት የኤንጂነር ግዛቸውን፣ የዶር. ኃይሉ አርአያንና የአቶ ዓሥራት ጣሴን ‹‹በታላላቅ›› ሰዎች ጥላ ስር ሆነው ለመሽሎክ ያቀዱት አልተሳካላቸውም፤ መማር የሚችሉት ሊማሩ ሄዱ፤ የማይችሉት ቀሩ።

---

# ዳግማዊ አፄ ቴዎሮስና ዳግማዊዎቹ እኛ

ዓለማየሁ ገላጋይ


በወጣኒነቴ፣ በድሜዬ አፍላ ጀንበር
የሊቅ የጣዲቁን፣ ሁለገብ ሐተታ አዘወትር ነበር
እና ምን ተረፈኝ
ተመልሼ ወጣሁ በገባሁበት በር።

ይሄ ግጥም የፋርሱ ባለቅኔ የዑማር ሀያም ሩብ አያት ነው። በዕውቀቱ ስዩም ግጥሙን ተርጉሞ ለ‹‹መግባትና መውጣት›› መጽሐፉ መግቢያ አድርጎት ነበር። ላለፈው ለዚህ ጋዜጣ መከራከሪያ ፅሁፉም ልከኛ መግቢያ ነው። ‹‹ተመልሼ ወጣሁ በገባሁበት በር›› ብሏልና።


በዕውቀቱ ስዩም በወረራ ከያዘው የክርክር መድረክ መልቀቁን ነጋሪት እያስጐሰመ ያውጅ እንጂ የሀሳብ ማፈግፈግ አልታየበትም። በአካል የለቀቀውን ክርክር መንፈሱ እንዲገዛለት በማሰብ አንዳንድ ግራ አጋቢ አቋሞቹን እየሸሸ የኗልዮሽ ወርውሯል። የኗልዮሽ ውርወራው ሲሻው ያቁስል፣ ሲሻው ይግደል በዕውቀቱን ግድ የሚሰጠው አይመስልም። ኢላማ ከሌላቸው አላማዎቹ ውስጥ የፅሁፉ ርዕስ እስከመሆን የበቃው ግርንቢጥ ሐሳብ ዋነኛው ነው። ‹‹ከህይወት የሚበልጥ ዓላማ የለም›› ይላል የበዕውቀቱ ገዢ ጭብጥ። እንዴት? በምን ምክንያት ህይወት ከዓላማ በላይ ተደርጐ ታየ? ዓላማ ውስጥ እኮ ሀገር፣ ወገን፣ እምነት… አለ። ህይወት ከእነዚህ ሁሉ ይበልጣል? እንዴት? ሀገር ውስጥ ነፃነት፣ ወገን ውስጥ ኩራት፣ እምነት ውስጥ ደግሞ ፈጣሪ የሉም? ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ህይወት በልጦ መገኘቱ በምን ነው?

እንደ በዕውቀቱ ‹‹መፈክር›› ከሆነ አቡነ ጴጥሮስ በፋሽስት ጥይት ተደብድበው መሞት አልነበረባቸውም፣ ባልቻ አባነፍሶ ህይወታቸውን አትርፈው ዓላማቸውን መግደል ነበረባቸው፣ አፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን የመስጠት አማራጭ ሊቀበሉ ይገባ ነበር… ከህይወት የሚበልጥ አላማ የለማ!! የበዕውቀቱ ‹‹መፈክር›› ‹‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል›› አይነት ነው። ይሄን ለመረዳት እሩቅ ሳይሄዱ የእጅጋየሁ ሽባባውን (ጂጂ) ‹‹አድዋ›› ዘፈን ማድመጥ ይበቃል። ‹‹ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ›› ትላለች።

‹‹ለተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነፃነት
ሰው ተከፍሎበታል በደምና በአጥንት››
ዓላማ ህይወት ነው፤ ህይወት ግን ሌጣውን



197



ለናፖሊዮን ፫ኛ የተላከ የአገው ንጉሤ ወልደሚካኤል ደብዳቤ።

198

አላማ ሊሆን አይችልም። ፍሬ ወድቆ እንዲያፈራ እንዲሁ የሰው ልጆች የትውልድ ቅብብሎሽ አንዱ በመሞቱ የሌላውን ህይወት እየተቤዠ ነው እዚህ የደረሰው። በዕውቀቱ የተገነዘበው እንዲያ አይደለም። ቃል በቃል ‹‹ግፍ›› ይለዋል። ‹‹ግፉን የክብር ልብስ በማልበስ ግፍን ከባህላችን ማስወገድ አንችልም።›› በዕውቀቱ አወቀውም አላወቀውም ‹‹የግፍ ሥራ›› አላማና ምክንያት የለሽ መጥፎ ተግባርን የሚወክል ቃል ነው። በአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ውስጥ ያለምክንያትና ያለአላማ እንዲህ ያለ መጥፎ ተግባር ተከናወነ የሚለው ነገር ካለ እሱን በመጠቆም ነበር ወደዚህ ድምዳሜ መድረስ የነበረበት። በዕውቀቱ ግን ማሳያ ከሌለው ድምዳሜው በመቀጠል እስካሁን ያጨቃጨቀንን ግርንቢጥ አቋሙን የኗልዮሽ ይወረውርልናል ‹‹እቅጩን ለመናገር ከህይወት የሚሻል ዓላማ በዚህ አለም ላይ የለም።››

በዕውቀቱ ይሄን መፈክሩን እንደዘበት ይወርውረው እንጂ የሶስቱም ፅሁፎቹ ማጠንጠኛ እንዝርት ሆኖ አገልግሎታል። ለምሳሌ ገና በመጀመሪያ መከራከሪያ ፅሁፉ ውስጥ አገው ንጉሴን (ንጉሴ ወልደሚካኤል) አንስቷል። አገው ንጉሴ በዕውቀቱ ‹‹ከህይወት የሚሻል ዓላማ በዚህ ዓለም ላይ የለም።›› ለሚልበት አቋሙ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ነው ያቀረባቸው። በመደምደሚያው ላይ ‹‹በኔ ግምት ያገው ንጉሴ ትልቅነት ገናናውን ልማድና ፍትሃ ነገስቱን ቸል ብሎ የገዛ ልቦናውን ለማድመጥ መድፈሩ ነው… ያገው ንጉሴ የሞራል ሐሳብ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመን ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከዛሬይቱ ኢራንና ሳኡዲ አረቢያ ጋር ሲነፃፀር እጅግ የቀደመ ነበር ማለት ይቻላል።››

የበዕውቀቱ ዋነኛ ችግር ነገሮችን ከአገርና ከወገን አላማ ነጥሎ ለመዳኘት መፍጠን ነው። አገው ንጉሴን ከአገርና ከወገን መለኪያ ውጭ ከተመለከቱ በዕውቀቱ የደረሰበት ድምዳሜ ላይ መድረስ የግድ ነው። አገው ንጉሴ በዕውቀቱ እንዳለው የአፄ ቴዎድሮስ ተቃዋሚ ብቻ ሳይሆኑ የመላው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ጠላት ነበሩ ማለት ይቻላል። አገው ንጉሴ እና ወንድማቸው ቀደም ሲል የአፄ ቴዎድሮስ ሎሌዎች ነበሩ። ሸፍተው እራሳቸውን ካዳራጁ በኋላ የትግሬን ገዢ ደጃች ኃይለማርያም አባ ጎርፌ (የራስ አርአያን ወንድም) ወግተው በመግደል ትግሬን ጠቅልለው ያዙ። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው የአጼ ቴዎድሮስ ተገዳዳሪ የሆኑት። አፄ ቴዎድሮስን ለማሸነፍ ከቱርክ እና ከፈረንሳይ ጋር መፃፃፍ ጀመሩ። መደራደሪያ ድርጎአቸው ደግሞ መላው ኢትዮጵያን ለቅኝ-ግዛት አሳልፎ የሚሰጥ ነበር። ለምሳሌ ለፈረንሳይ ንጉስ ነገሥት ለሣልሳዊ ናፖሊዮን የፃፉትን ደብዳቤ ቆንፅለን እንመልከት።

‹‹ንጉሠ ነገሥት ሆይ።

‹‹….የእንግሊዞችን ተንኰል አውቃለሁ። ቆንስላቸውን ቴዎድሮስ በሉኝ ወደሚል ቋረኛ ካሳ መስደዳቸውን አውቃለሁ። ክፋታቸው ሳይበዛ በጭንቅ ጊዜ ልቤን ወደርስዎ የፈረንሲስ ንጉሠ ነገሥት አድርጌአለሁ። አድርጌም ከርስዎ የኢጣሊያን አርነት ጠባቂ በታላቅ ኃይልዎ ያገሬን አርነት እንዲጠብቁልኝ የሥራት ብርሃንም ወዳገሬ እንዲያደርሱልኝ ከዘራፊ ቴዎድሮስ እጅ እንዲጠብቁልኝ እለምንዎአለሁ። ይህንንም እንዲፈፀም ሁለት ነገር ያስፈልጋል። በፊት እንደላክሁብዎ ሥራትን ሁሉ የሚያይ የርስዎ ምስለኔ ቢሰዱልኝ በአገሬ እንደራሴ የፈረንሳዊ ባንዴራንም አስተክላለሁ።

ሁለተኛው እኔ የምመኘው እርሱ ነውና ሁለት ባተርያ የመድፍ ከነተኳሹ ጋራ ነው። ስለሚያደርጉልኝ ነገር ደስ አሰኘዎ አለሁ ብዬ ተስፋ አለኝ። ስላደረጉልኝና የስዊስን መንገድ ባሕርዎ በመግጠም ላገሬ ስለሚያደርጉልኝ ራስ ዱማራ የሚባል ዙላን አበርክትዎ አለሁ። ንጉሰ ነገስት ሆይ የነገርሁዎ የልቤን ሐሳብ ቶሎ እንዲፈፅሙልኝ ተስፋ አለኝ።›› የአገው ንጉሴ አገር አጠቃሽ አደጋዎች እነዚህ ናቸው፡-

ሀ. ፈረንሳይን የአገር አርነት ጠባቂ አድርጐ መሾም (የሞግዚት አስተዳደር)

ለ. አሻንጉሊት መንግስት ሆኖ በፈረንሳይ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ምስለኔ ስር ለመታዘዝ መፍቀድ

ሐ. ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያውያን አጥብቀው የሚጠሉትን የባዕድ ባንዲራ በአገር ውስጥ ማውለብለብ ግዴታ መቀበል

መ. መሬት (ራስ- ዱማራ- ዙላን) መስጠት

የበዕውቀቱ ታላቅ፣ አገው ንጉሴ በእነዚህ ነጥቦች ለመደራደር ሐሳብ፣ አቀረቡ እንጂ ከወደፈረንሳይ ከዚህም የባሰ ድርድር ቢቀርብ ላለመቀበል ያሳዩት ክልከላ የለም። እኒህ ቅኝ ተገዢነትን የሚቃብዙ መኳንንት ፈረንሳይን ለማስደሰት ሲሉ የእጅና የእግር መቆረጥን

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

# ከነዳጅ ፍለጋ በፊት ፖለቲካዊ ማሻሻያ ይቀድማል

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ባለፈው ሳምንት ታላቅ አለም-አቀፋዊ ስብሰባ አስተናግዳለች፡፡ በዚህ የዓለም የኢኮኖሚ ፎረም የአፍሪካ ስብሰባ ከመጀመሩ አንድ ቀን ቀደም ብሎም የሀገር ውስጥ እና የውጭ የንግድ ድርጅት ተወካዮች የተገኙበት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ፎረም ተካሂዷል፡፡ በዚህ የፎረሙ ስብሰባ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ነዳጅ ልታገኝ እንደምትችል ጥቁምታ ሰጥተዋል፡፡

ፍትህ ይህ ዜና እውነት ነው አይደለም የሚለው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን በጥንቃቄ መመልከት አለብን የሚል አቋም አላት፡፡ የዚህ አቋማችን መነሻ ግልፅ ነው፡፡ ሌሎች እኛን መሰል የአፍሪካ ሀገራት ነዳጅን ባገኙ ማግስት የዜጎቻቸው ፍንደቃ ወደ ብሄራዊ ሀዘን ሲቀየር ታዝበናል፡፡ የዚህ ሀገራዊ መከራ መነሾ ሀገራቱ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ባለመገንባታቸው እና የፖለቲካ ምህዳሩን የመዘጋታቸው ሁኔታ ከነዳጁ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ ለፖለቲካዊ ስልጣናቸው ማደላደያነት ብቻ እንዲጠቀሙ ስለማድረጋቸው ነው፡፡

እናም ይህንን ‹‹በረከት›› ተከትሎ በስልጣን ላይ ያሉት የሚቃወሟቸውን ለመደለል ሲብስም ሀገራዊ ገቢን ለወታደራዊ እና የደህንነት ተቋማት መጠናከር ማዋላቸው ተደጋጋሚ የሀገራቱ መለዮ እንደሆነ ያየነው ሃቅ ነው፡፡ ይህን ኢ-ፍትሃዊ የመንግስት ድርጊት መቃወምን አስቸጋሪ የሚያደርገው ደግሞ በሀገራቱ ያለው ጥልቅ አምባገነንነት መሆኑ የአደባባይ እውነት ነው፡፡ ፍትህ የተፈጥሮ ሀብቱ በተባለበት አጭር ጊዜ ውስጥ ቢገኝ በሌሎች ሀገራት ያየናቸው አደጋዎች በኢትዮጵያም ላለመከሰታቸው ምን ዋስትና አለን? ስትል አጥብቃ ትጠይቃለች፡፡

ነዳጅ ይገኝባቸዋል የተባሉት ሁለቱ የሀገራችን ክፍሎች ብዙም የሚያስመካ ፖለቲካዊ መረጋጋት እንደሌላቸው በሰላማዊ ዜጎች ላይ በሚደርሱ የሽብር ጥቃት ያየነው ነውና፡፡ የኡጋዴን ክልል ለጋዜጠኞችም ሆነ ለአጥኚዎች ብዙም የተመቸ ባለመሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ስለነዳጅ ሀብቱ ያላቸውን አመለካከት ማወቅ አዳጋች ሆኗል፡፡ ከዚህ ቀደም በአንድ ነዳጅ ፍለጋ ላይ በተሰማራ ኩባንያ ሰራተኞች ላይ አደጋ በመድረሱ ከሁሉ አስቀድሞ መንግስት በአካባቢው ያለው የሰላም ሁኔታ አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል ብላ ፍትህ ታምናለች፡፡

ቁጥራቸው የበዛ በሀገራችንን ፖለቲካ ላይ ምርምር ያደረጉ ምሁራኖች ኡጋዴንን በመጥቀስ ማዕከላዊ መንግስቱ የቁጥጥር አቅሙ እጅግ መላላት እንደጀመረ እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚጠቀስ መረጋጋት በሌለባቸው ክልሎች የሚገኘው ነዳጅ የእርስ በእርስ ግጭት መንስኤ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ስላለ መንግስት ጉዳዩን እንዲያስብበት ፍትህ አበክራ ትጠይቃለች፡፡

የነዳጅ ሀብቱ ይገኝባታል የተባለችው ሌላዋ የሀገራችን ክፍል ጋምቤላም ከኡጋዴን ጋር የሚመሳሰሉ ተሞክሮዎች አሏት፡፡ ለኢንቨስትመንት በሚል መንግስት ለውጭ ባለሃብቶች የሰጠውን ሰፋፊ የእርሻ መሬት ተከትሎ በአንዳንድ የክልሉ ነዋሪዎች እየተስፋፋ ያለው ቅሬታ እና በባዕዳኑ ላይ የሚፈፀሙት ጥቃቶች መባባስ መነሻ ምክንያት ስር-ነቀል መፍትሄ ሳይፈለግለት ወደ ነዳጅ ፍለጋው መሄድ ግጭቶችን ሊቀሰቅስ ይችላልና መንግስት ከዚህ ስጋት የሚያድን ፍትሃዊ እርምጃ ይወስድ ዘንድ ፍትህ ትጠይቃለች፡፡

እንደ ፍትህ እምነት ይህን የተፈጥሮ ሀብት መገኘት ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሀገራዊ ጉዳዮችን ለመከላከልም ሆነ ለመቀነስ መፍትሔው አፋጣኝ ፖለቲካዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ነው፡፡ መንግስት የተቋማትን ነፃነት ካልጠበቀ፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ለአማራጭ ድምፆች ክፍት ካላደረገ እንዲሁም በሁለቱ የሀገሪቱ አካባቢዎች መሰረታዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ማሻሻያዎችን ካልከወነ አደጋው መኖሩ አይቀሬ ነውና ከነዳጅ ፍለጋ በፊት ፖለቲካዊ ማሻሻያ ሊቀድም ይገባል ስትል ፍትህ ደግማ ደጋግማ ታስጠነቅቃለች፡፡

## አስተያየት

**ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**
**ጽህፈት ቤት የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ዳይሬክቶሬት**
**የተሰጠ ማስተባበያ**

# የፓርላማ አሠራርና የፍትህ ወቀሳ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም....

ሚያዝያ 12 ቀን 2004 ዓ.ም. የወጣው የፍትሕ ጋዜጣ ‹‹የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራርያ የቱን ጥያቄ መልሷል?›› በሚል ርዕስ ያስነበበው ፅሁፍ የፓርላማውን የስራ እንቅስቃሴ በትክክል የማይገልፅ በመሆኑ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ዳይሬክቶሬት ምላሽ ሰጥቶበታል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ-መንግስቱ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት አንዱ የአስፈፃሚውን አካል አሰራር መቆጣጠርና መከታተል ነው፡፡ የዚህ ስልጣን መተግበሪያ ከሆኑ በርካታ ስልቶች አንዱ የምክር ቤት አባላት ለሚኒስትሮች እና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄዎች እያቀረቡ በቃል መልስ የሚሰጥበት የጥያቄ ጊዜ ነው፡፡ ይህም በም/ቤቱ ደንብ ቁጥር 3/98 በአንቀጽ 87 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ደንቡን መሠረት አድርገው የምክር ቤት አባላት በፈለጉት ጉዳይ ላይ ጥያቄያቸውን ለሚኒስትሮች ወይም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እያቀረቡ በቃል ማብራሪያ እየተሰጠባቸው ስላነሱት ጉዳይ ትክክለኛውን ግንዛቤ ይይዛሉ፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. የሰጡት ማብራሪያ የዚሁ የም/ቤቱ የቁጥጥርና ክትትል ተግባር አካል ነው፡፡

ይህን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ አድርጎ ፍትሕ ጋዜጣ ከምክር ቤት አባላት የተነሱ ጥያቄዎች ቅድሚያ ለማይሰጣቸው ጉዳዮች ትኩረት መስጠታቸው አግባብ እንዳልሆነ በመዘገብ የምክር ቤቱን አባላት ወቅሷል፡፡

የፍትሕ ጋዜጣ ወቀሳ የቱን የሕግ ማዕቀፍ መሰረት አድርጎ እንደሆነ ግራ ከማጋባቱ ባለፈ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 590/2000 ዓ.ም. ትክክለኛ ነገር ተዘግቦ ለህዝብ እንዲደርስና ዘገባውም የሰውን ክብርና መልካም ስም እንዳይጎዳ የሚለውን ይፃረራል፡፡ ፍትሕ ጋዜጣ ያነሳቸው አስተያየቶች ከዚህ የአዋጁ መርህም ሆነ በሕገ መንግስቱ የማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብቱ እንዲጠበቅ ከደነገገው ከአንቀፅ 24 ጋርም ጭምር የማይሄዱ መሆናቸውን ፍትሕ ጋዜጣ ካነሳቸው ጥቂቶቹን ወስዶ ማየት ይቻላል፡፡

የኑሮ ውድነት እያለ ስለሩቅ ምስራቅ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ንድፈ ሃሳብ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ ይመከርበታል የሚለው አንዱ የአስተያየቱ ነጥብ ነው፡፡ የሩቅ ምስራቅ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በጎ እንደሆነ የኢኮኖሚ ቀውስ የደረሰባቸው ሀብታም አገሮችና ከነሱም በኢኮኖሚው ቁንጮ የሆነችው አሜሪካም ጭምር የሩቅ ምስራቅ ኢኮኖሚያዊ እድገት እየመጠቀ መምጣቱ የምስክርነት ቃል መስጠታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የዚህ ኢኮኖሚ ንድፈ ሃሳብ ተተንትኖ በተግባር ሲታይ በዕድገት ብራዚል የእንግሊዝን ቻይና ደግሞ የጃፓንን ቦታ እንደያዙ ሁሉ እኛም በዚህ ዙሪያ ደረጃችንን ለማሻሻል መምከሩ እና ልማታችንን ለማፋጠን የሚረዱ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመውሰድ መወያየቱ እንደ ችግር ማንሳቱ ተገቢ አይደለም፡፡

እንደ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን አስመልክቶ በም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤም ሆነ በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ ብዙ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በመካሄድም ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ከንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክና ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጋር ስለመሰረታዊ ሸቀጦች ዋጋ ትመና ተፈፃሚነት፣ ከውጭ አገር ተገዝተው የሚገቡ የስኳር፣ የዘይትና የስንዴ ዋጋ ከዝቅተኛው ሕብረተሰብ ክፍል የመግዛት አቅም ጋር ስለመጣጣሙና ስለስርጭቱ ጉዳይ፣ ስለባንክ ወለድ ምጣኔና ባንኮች ገንዘብ ስለሚይዙበት፣ በኮንትሮባንድ ንግድና በሕገ ወጥ መንገድ ሸቀጥ በሚያከማቹ ነጋዴዎች ላይ መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በስፋት ተመክሮባቸዋል፡፡ ችግሩ እስከሚቃለል ድረስ መመካከሩ ይቀጥላል፡፡ የኑሮ ውድነት ጉዳይ በፓርላማ ቅድሚያ አልተሰጠውም የሚለው የፍትሕ ጋዜጣ አስተያየት ከእውነት የራቀ ነው፡፡ ዕድገቱም ሆነ የኑሮ ውድነቱ ጉዳይ የፓርላማው የቅድሚያ አጀንዳ ሆነው ትላንትም ዛሬም ይመከርባቸዋል፡፡

ሌላው በአረብ አገራት ከሚንገላቱትና ከሚሰቃዩት ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን የኤርትራ ተወላጆች ጉዳይ በፓርላማ ቅድሚያ ቦታ ይሰጣል የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በአረብ አገራት በዜጎች ላይ የሚደርሰው እንግልትና ስቃይ በፓርላማው ትኩረት አልተነፈገውም፡፡ ለሥራ ፍለጋ ወደ አረብ አገራት የሚደረገው ጉዞ ስርዓት እና ዋስትና ያለው እንዲሆን ላኪዎች ተጠያቂነትን በተላበሰ ሁኔታ ስራቸውን እንዲያከናውኑ የግል ሰራተኞችና አሰሪ አገናኝ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ በማውጣት እንግልቱ የሚቀረፍበት ሁኔታ አመቻችቷል፡፡

ሌላው ኤምባሲ በሌለባቸው አገሮችም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የቆንፅላ ጽ/ቤት እንዲቋቋምና ከመንግስታቱ ጋር መልካም ወዳጅነት በመፍጠር መብታቸው እንዲከበር ጥረት አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል ስደተኞችን በሕገ ወጥ መንገድ በየብስ፣ በአየርና በባህር የማስወጣትና ማስገባትን የሚከለክለውን ፕሮቶኮልና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በተለይም የሴቶችና የሕፃናት ዝውውርን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና የወንጀሉን ፈፃሚዎች ለመቅጣት የወጣውን ዓለም አቀፍ ፕሮቶኮል ምክር ቤቱ የአገሪቱ ሕግ አካል እንዲሆኑ አፅድቋል፡፡

ወደ ገፅ 13 ዞሯል ≫

## ለአዘጋጁ የተላከ መልእክት

ለአቶ ተመስገን ደሳለኝ
የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ
የዓለማየሁና የበእውቀቱ ክርክር

ሁለቱም የሚሉትን ብለው ሳይረታቱ፣ እኛንም በሀሳባቸውም ሆነ በአስተሳሰባቸው ሳያሻሽሉን የጀመሩትን ክርክር ቁርጥ አድርገው ሲተውት ለእኔ ታሪካዊ ሕመማችንን የሚያሳይ ነው፤ ስለዚህ ከሕመሙ መገላገሌን ለማሳየትም ቢሆን ክርክሩ ውስጥ ሳልገባ በፍሬ ነገሩ ላይ እምነቴን ልግለጽ፡፡

ዓለማየሁ ቴዎድሮስን በማወደስ ከብዙ ሰዎች ጋር ይሰለፋል፤ ከደርግም፣ በተለይ ከኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም ጋር፣ ከወያኔም ጋርና ሌሎች የኢትዮጵያን አንድነት ከቴዎድሮስ ጋር ከሚያቆራኙ ሰዎች ጋር ይሰለፋል፤ ምሳሌዎቹን ሆን ብዬ የጠቀስሁት ዓለማየሁን ለማሸማቀቅ ሳይሆን በኢትዮጵያ አንድነት ስም ቴዎድሮስን አስቀድመው የሚሰለፉ ሰዎች ግፈኞችም መሆናቸውን ለማመልከት ነው፡፡

በፍልስፍና የቆየ ጥያቄ ነው፤ ለጥሩ ዓላማ ስንል አሰቃቂ ግፍን ሁሉ መፈጸም ክፋት የለውም፤ በእውቀቱ ለጥሩ ዓላማም ቢሆን ግፍን መፈጸም ክፉ ነው፤ የሚል ይመስላል፤ በአንጻሩ ዓለማየሁ ዓላማው ጥሩ ከሆነ ግፍ ክፋት የለበትም ባይ ይመስላል፡፡

በበኩሌ ለምንም ዓይነት ዓላማ ግፍ ክፉ ነው፤ ብዬ አምናለሁ፤ እኔ ለምቀበለው ዓላማ ግፍ ሲፈጸም እልል የምል፣ እኔ ለማልቀበለው ዓላማ ግፍ ሲፈጸም እሪ! የምል ከሆነ የኅሊናዬ ሚን ተሰብሮብኛል ማለት ነው፡፡

አክባሪዎ
መስፍን ወልደማርያም


# ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተሮች
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተር
ሰውዓለም ታዬ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ
አናንያ ሶሪ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡- አራዳ
ቀበሌ፡- 17
የቤት፡- 984

# የግል ፕሬስ አሳታሚዎች ማተሚያ ቤቶች ያቀረቡትን ውል ቅድመ ምርመራ ነው በሚል ተቃወሙት

ጋዜጦችና መጽሔቶችን የሚያትሙ ማተሚያ ቤቶች ለግል ጋዜጦችና መጽሔቶች አሳታሚዎች የላኩት የሕትመት ውል ቅድመ ምርመራን (Censorship) አንግሶ ሕገ መንግስቱንና የፕሬስ ነፃነትን የሚፃረር ነው ሲሉ አሳታሚዎቹ ተቃውመውታል፡፡ አቤቱታቸውንም ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊና ለአታሚዎቹ አቅርበዋል፡፡

አሳታሚዎቹ የሕትመት ‹‹ስታንዳርድ›› ውል ረቂቅ አዋጅ ቅጂ ከደረሳቸው በኋላ በተናጠል ሳይሆን በጋራ አቋም ለመያዝ በተደጋጋሚ ተሰብስበዋል፡፡ በስብሰባቸው ላይ እንደዚህ ዓይነት ውል እንዲፈርሙ የተላከው ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ ከቦሌ ማተሚያ ቤትና ከሌሎችም መሆኑን ተገንዝበዋል፡፡

ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ባቀረቡት የአቤቱታ ደብዳቤ በሌሎች ማተሚያ ቤቶች የሚያሳትሙ አሳታሚዎችም በጋራ ያሉበት ሲሆን፣ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የተላከውን ግን እዚያው ለሚያሳትሙ አሳታሚዎች ነው፡፡

አሳታሚዎቹ በወሰዱት አቋም እንዲፈርሙ ከተላከላቸው የውል ረቂቅ ውስጥ እጅግ ያሳሰቡዋቸው አንቀጽ 10 ላይ የሰፈሩት ሐሳቦች ናቸው፡፡

### አንቀጽ 10
### ሕግን የተላለፈ ይዘትን አለማተም

አታሚው በአሳታሚው እንዲታተም የቀረበለት የፅሑፍ ስክሪፕት ሕግን የሚተላለፍ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ካለው አላትምም የማለት መብት አለው፣ አታሚው አሳታሚው የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የሕትመት ይዘት የማውጣት ዝንባሌ ያለው መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው በማንኛውም ጊዜ ውሉን ለማቋረጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡

በእዚ አንቀጽ የሰፈሩት ሐሳቦች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 ላይ ቅድመ ምርመራ በማናቸውም ሁኔታ የተከለከለ ነው የሚለውን የሚፃረሩ በመሆናቸው ውሉን መፈረም ሕገ መንግስቱን በመፃረሩ ቅድመ ምርመራን መቀበል ነው ብለው በማመን ድርጊቱን በጥብቅ ተቃውመዋል፡፡ አሳታሚዎቹ ከውሉ ቅድመ ምርመራ ይዘት በተጨማሪ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ቀጠሮ ከያዘ በኋላ ስብሰባውን ወደ ጎን በመተው፣ ሁለት ሳምንት ሙሉ በስልክና በደብዳቤ ‹‹መጥታችሁ ካልፈረማችሁ የሕትመት ውጤታችሁ አይታተምም›› በማለቱ በአሳታሚዎቹ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታና ትዝብት አስከትሏል፡፡

አሳታሚዎቹ ባደረጉት ስብሰባ ችግር ሲኖር ከመሰብሰብ ይልቅ ቋሚ የሆነ የአሳታሚዎች ማኅበር የመመስረትን አስፈላጊነት በማመን የምሥረታ እንቅስቃሴው እንዲጀመር ወስነዋል፡፡

በተጨማሪም በቅድመ ምርመራ መልክ የመጣውን የውል ረቂቅ አሳታሚዎች ቢቃወሙትም፣ ሚዲያውም ራሱ ከሕግ ጥሰትና ከሥነ-ምግባር ጉድለት መታቀብና መጠንቀቅ እንዳለበት ያምናል፡፡ ሚዲያው የራሱን ጉድለት በማየትና በሕዝብ የሚቀርብለትን አቤቱታ እያስተናገደ፣ እንዲያስተካክልና እንዲጠናከር ለማድረግ የተጀመረው የሚዲያ ‹ካውንስል› ምሥረታ ሒደት በአስቸኳይ ተጠናቆ ጉባዔው እውን እንዲሆን ወስኗል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የፕሬስ ውጤቶች እየደረሰባቸው ያለው አደጋ የራሳቸው ማተሚያ ቤት ስለሌላቸውና አብዛኞቹ በመንግስት ማተሚያ ቤት ስለሚያሳትሙ ነው፡፡ አሳታሚዎቹም ይህንን በመረዳት ለወደፊቱ በጋራ ተጋግዘውና ተደጋግፈው የጋራ ማተሚያ ቤት ለማቋቋም ተስማምተዋል፡፡ በመጨረሻም ይህ ዜና የጋራ ሆኖ በጋዜጦች ለሕዝቡ እንዲሰራጭ ተስማምተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ነዳጅ

... ከገፅ 2 የዞረ

በነዳጅ መገኘት እና በኢኮኖሚ ዕድገት መሀከል አለ የሚባለውን ተመጋጋቢ ዝምድና የማይቀበሉ ፀሐፊዎች ለዚህ በምክንያትነት የሚያነሱት በተለምዶ ‹‹የደች ህመም›› ተብሎ የሚጠራውን መከራከሪያ እና የናይጄሪያን ተሞክሮ ነው፡፡ ሀገራት ነዳጅ ባገኙ ማግስት የብሔራዊ ገንዘባቸው አቅም ከፍ እያለ ይመጣል፡፡ የገንዘብ አቅሙ እየጨመረ መምጣት ሀገራቱ ወደ ውጪ ይልኳቸው የነበሩት የግብርና እና ሌሎች ሀገራዊ ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖራቸውን መሸጫ ዋጋ እጅግ ያንራል፡፡ የዚህ ቀጥተኛ መዘዝ ሀገር በቀል ኤክስፖርተሮችን አቅም ማዳከም እና ህልውናቸውን በእርሻ ላይ ያደረጉ የንግድ ተቋማትንም ሆነ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጐችን ዕጣ ፈንታ አጣብቂኝ ውስጥ የሚከት ይሆናል፡፡ በፀሐፊዎቹ ‹‹የደች ህመም›› ተብሎ በሚጠራው በዚህ ክስተት የተነሳም እነዚህ ሀገራት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚሆኗቸውን ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገቡ ይገደዳሉ፡፡ የውስጡን በመተካት ወደ ሀገር እንዲያስገቡ ይገደዳሉ፡፡ ፕ/ር ቤንጃሚን ስሚ እንደሚጠቅሱት ይህ ሁነት በተራዛሚው ኢኮኖሚያዊ መቀዛቀዝን ይፈጥራል፡፡

የነዳጅ ሀብቷ ግጭቶችን ከማባባስ ባለፈ የሚጠበቀውን ያህል ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዳላመጣላት የምትጠቀሰው ናይጄሪያ፤ ነዳጅ መገኘት ብቻውን ሀገራዊ ፋይዳ አለው ብለው ለሚከራከሩት በመሞገቻነት የምትነሳ ሀገር ሆናለች፡፡ እ.ኤ.አ. በ1965 ዓ.ም. ከነዳጅ የተገኘው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 33 ዶላር የነበረ ሲሆን፤ ከሀገራዊ ጠቅላላ የኢኮኖሚ እድገት በነፍስ ወከፍ ደረጃ የነበረው መጠን 245 ዶላር ያህል ቢሆንም፤ እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ም. የመጀመሪያው የነዳጁ የገቢ ድርሻ ወደ 325 ዶላር ሲያድግ፤ ለሀገራዊ ጠቅላላ የኢኮኖሚ እድገቱ በነፍስ ወከፍ ደረጃ ያለው መጠን በተፃራሪው በነበረበት ቆሟል፡፡ ከነዚህ ቁጥራዊ ጭብጦች በተጨማሪ በጥልቅ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ ዜጐች ቁጥር ወደ 70% ንሯል፡፡ ለዚህ ኢኮኖሚያዊ ድቀት በሀብቱ የተጠቀሙት ጥቂት የፖለቲካው ልሂቃን መሆናቸው እንደሆነ የሚያነሱት አዴርጆ አይፋሱ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው እንደሚያወሱት እ.ኤ.አ ከ1965 ዓ.ም. እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 35 ዓመታት ከሀገሪቱ የወጣው ነዳጅ ግጭቶችን ከመቀስቀሱ ውጪ በዜጐች የኑሮ ሁኔታ ላይ አንዳችም በጎ አስተዋፅኦ አላደረገም፡፡

### ኡጋዴንን እንደ ሞዴል

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው አገር-በቀል የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ ኩባንያ የሆነው ሳውዝ ዌስት ኢነርጂም ሆነ ፔትሮናስ (ፔትሮሊየም ናሲናል ብርሃድ) የተፈጥሮ የጋዝ ክምችት አሉባቸው ብለው ስራ ከጀመሩባቸው ክልሎች መካከል የኡጋዴን አካባቢ አንዱ ነው፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት በአካባቢው የደረሰው የፔትሮናስ ሰራተኞች ግድያ ዜናን ተከትሎ ብዙም ሳይቆይ ለድርጅቱ በኮንትራክተርነት ይሰራ የነበረ እንግሊዛዊ መገደሉ የክልሉን ነዳጅ-ተኮር ለሆነ ኢንቨስትመንት ያለውን ምቹነት ጥያቄ ውስጥ ከቶታል፡፡ የብሉምበርጉ ዘጋቢ ጃሶን ማክለር በወቅቱ እንዳተተው አቶ በረከት ስምኦን ጉዳዩን ‹‹ሽፍትነት›› ቢሉትም፤ ለጥቂት ጊዜያትም ቢሆን ፔትሮናስ የተባለው ኩባንያ ክልሉን ለቆ ወጥቷል፡፡ በጋምቤላ ስላለው ነዳጁን ለማውጣት ምቹ የመሆን ወይም ያለመሆን ጉዳይ ጥናቶች ባይኖሩም፣ ጀምስ ቦሸፍ የተባሉ አጥኚ በኡጋዴን ላይ የሰሩት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ይህን ክፍተት በከፊልም ቢሆን ይሞላል፡፡

ስለነዳጅ ፍለጋ ጉዳይ የሚያነሱ ፀሐፊዎች በኢንቨስትመንቱ ላይ የሚሳተፉ ድርጅቶች ‹‹የፖለቲካ አደጋ ትንተና›› ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ትንተና ስለማዕከላዊ መንግስቱ የፖለቲካ አረዳድና ታሪካዊ ክንውኖች፣ ተሳታፊ የፖለቲካ ቡድኖች ነዳጅን በተመለከተ ያላቸውን ምልከታ እና የሀገሪቱን አጠቃይ የፖለቲካ ስርዓትም ሆነ ነዳጅ በተገኘበት አካባቢ ያለውን ፖለቲካዊ ጥምዝምዞሽ አካትቶ ይይዛል፡፡ ጀምስ ቦሸፍ “Investing in troubled territories; Industry specific political risk analysis and the oil and gas Industry” በሚለው በቀደመው ዓመት በታተመው ጥናታዊ ስራቸው የኡጋዴንን ጥያቄ የተፈጥሮ ሀብትንም ማዕከል ያደረገ አድርገው አቅርበውታል፡፡ ለጉዳዩ ቅርበት ለሌለው ሰው ብዙም በማይገቡ፤ የቢሆን አደጋ መተንተኛ ሞዴሎች በመጠቀም እንደሚገልፁት ‹‹ካሉት የእርከን ደረጃዎች ኡጋዴን እጅግ ከፍተኛ አደጋ እንደሚከሰት በሚነግረው እርከን /ከ61-80/መሀከል በማረፏ/67.4 በማግኘት›› በአካባቢው ነዳጅን በተመለከተ ኢንቨስት ለማድረግ መሞከር ሰዋዊ እና ቁሳዊ ጉዳቶችን ሊያስከትል ይቻላል፡፡ እንደ አጥኚው ሙግት፡- በአካባቢው ያለው መንግስታዊ የቁጥጥር አቅም አነስተኛ መሆን፣ አልፎም ያልተረጋጋ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስርዓት መኖር የአካባቢውን ለኢንቨስትመንት ምቹ ያለመሆን አባብሶታል፡፡

# በመስመር መካከል

... ከገፅ 11 የዞረ

ይለናል ቀሪጦን የተባለ ፀሐፊ፡፡ (ይህ ከአካዳሚው ወገን ነው)

2. የትውልድ ወገኗ ከቃኤል ወገን የሆነ… ኑሄም የምትባል ሴት ነበረች፡፡… ይህች ሴት ከሴቶች ሁሉ ያማረችና ውብ ነበረች ይለናል… ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ…፡፡… ምንም እንኳ የቃኤል ዘሮች… አብዝተው ቆንጆ እንደነበሩ ብዙ መፃህፍት የገለፁ ቢሆንም… ‹ኑሄም› ግን ከሁሉ ትልቅ ነበር፡፡

ኑሄም… ውበቷ ከሽክላዋ ከፍ ያለ ነበር፡፡… ውስጧም ውብ ነበር… ለውጥ ፈላጊ እናም… ፈልጋም አልቀረች አገኘች… ወይም… ጀመረች… ፋሽንን (ዘመነኛ… አለባበስን)… ኑሄም የተለያየ ሕብረ ቀለማት ያለውን… ግምጃ… ሠራች… እንግዲህ ከአዳም ከ1932 ዓመት በኋላ… የተለያየ ህብረ… ቀለማት… ያላቸው ልብሶች…ዲዛይን ተደረጉ… በኑሄም…

3..እጅግ ታላቁና ገናናው የምድራችን… ጥበባዊ ገፀ በረከት የተነሳንበት ሃሳብን ከፍ የሚያደርገው የምድራችን የየትኛውም ስሜት መገለጫ የሆነው ሙዚቃ በዚህ ዘመን ተጀመረ ከአዳም ሶስተኛ በሚሆን በሄኖስ ዘመን በ1932 ዓመት፡፡

ዮቤድ የተባለ ሰው ‹‹ብዙ የቅኝት አውታሮች ያሉት መሰንቆን… ክራርን… ሠርቶ አሳየ፡፡ … ዮቤድ… የሙዚቃ መሳሪያዎቹን ብቻ አልነበረም የሰራው… ሙዚቃን ራሷንም ይጫወታት ጀመር… ክራሩን ይመታል… ይዘፍንማል…

ዮቤድ ሙዚቃ ሲጫወት ይለናል… ጊዮርጊስ ሌብን አልአሜዳ… ዮቤድ… ሲዘፍን… አውሬዎችና ወፎች… የመሰንቆውንና የርሱን ድምፅ ለመስማት… ይሰበሰቡ ነበር… ባላንጣ የሆኑ እኒህ ፍጥረታት አይጣሉም ነበር… አውሬ እንስሳትን አይተናኮልም… ወፎችም አራዊትን ፈርተው አይበሩም… እንስሳቱም… በአናብስቱ ግርማ አይደነግጡም… በ‹ዮቤድ› ሙዚቃ ይመሰጡ ነበር እንጂ…

ዮቤድ ሙዚቃን ከጀመራት በኋላ… የሰው ልጆ (ከሰው ልጅም የቃኤል ዘሮች… ምናልባትም… ነፍስ ገዳይነታቸውን ስለሚያባብልላቸው ይሆናል)… አላረፉም፡፡… ከመዝፈን አልቦዘኑም… ቀንም… ሌሊትም.. ነፍሳቸው… በሙዚቃ ደከመች… በዚህ ጊዜ… ከቃዔል ዘሮች ከፍ ብለው ለገነት ቀረብ ብለው ይኖሩ የነበሩ ቅዱሳኑና ንፁሃኑ… የሴት ልጆች… በነቃዔል ህይወት ተማረኩ… ከእነርሱም ወደ መቶ የሚጠጉት… የመላዕክትን ዝማሬ ከሚሰሙበት ከ‹ደብር ቅዱስ› ወደ ምድር ወረዱ በሉ..ጠጡ… ጨፈሩ… ከቃዔል ሴቶች ልጆች ጋር ተኙ… ተኙና… እረኞችን ወለዱ፡፡… ሲያልቅ አያምር እረኞችን ወለዱ፡፡… ይለናል… ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ… (ከመላዕክት ጓደኝነት ወደ እረኛነት)

እንግዲህ የሙዚቃ ነውርነት እዚህ ላይ ነው… የሙዚቃ ሃይልም.. እንዲሁ፡፡ ሙዚቃ ለመላዕክት ቅርብ የነበሩትን… የሰው ልጆች… እስትክትማርከ ድረስ… ሃይል በውስጧ አለ፡፡ በዚህ ምክንያት መልኩን እያጣ መጠኑን እያለፈ… የመጣው የሙዚቃ ፍቅር ወደ አስረሽ ምችው ሲቀየር… ዓለም ታላቁን ጥፋት… አስተናገደች፡፡ በሄኖስ ዘመን የተጀመረው… የአስረሽ ምችው የሙዚቃ ፍቅር… የአዳም አስረኛ በሚሆን በ‹ኖህ› ዘመን… የጥፋት ውሃን አስከትሏል… ምድር… ስምንት ሰው ብቻ… እስኪቀርባት ድረስ፡፡

ልናገር… የምሻው… ውጤቱን አይደለም… የነገሩን ሃይል እንጂ፡፡… የትኛውም ነገር ውስጥ የመጠንና የልክ ጥያቄ አለ፡፡… የመውደድ መጠንና ልክ የለውም፡፡ ..ግን.. የቱን ነው ያለ ልክ የምንወደው የሚለው ላይ… ጥያቄ ካለ… የአይነት ልክ፡፡ ሙዚቃ ስሜትን አትከተልም…ምርጥ… ሙዚቀኛም ያለውን አያወራም… ዝም ባልነው ውስጥ… መሆን ያለበትን ያዜማል እንጂ…

ዮቤድ… የሙዚቃ መሣሪያን የሚጫወት የምድራችን ተቀዳሚው ሙዚቀኛ ነበር፡፡ ምናልባት የቃኤል ልጆች የአባታቸው ነፍሰ-ገዳይነትን ለመርሳት… የአጎታቸውን ያለ ጊዜው ገና በወጣትነቱ መቀጠፍ (አቤል የሞተው በ300 ዓመቱ ነው)… በአዳም የመጣው የሞት መኖርን ለመርሳት… ይሆናል… የደነሱት… የጨፈሩት…የሞዘቁት… ‹‹ያኛውን ላለመስማት… የዚህን ድምፅ ማጉላት››… ከኋላቸው ያለው… የአባታቸውን የግፍ ሳውንድ ትራክ ላለማዳመጥ… የዮቤድን.. ዋሽንት… መረጡ ሰዎቹም… አራዊቱም… ወፎቹም… እንስሳቱም እንዲህ እያሉ… የመጀመሪያውን… ሙዚቃ ጀመሩ…

‹‹ምነው ተታለለ… እግዜር የሰማዩ…<br>
ምነው… ተራገመ እግዜር የሰማዩ…<br>
አዳም አይደለም ወይ… የሰው ልጅ ገዳዩ…<br>
…<br>
ቃኤልን ሲራገም እግዚአብሔርን ስሙ<br>
በአዳም አይደለም ወይ… ያ’ቤልማ ደሙ…<br>
በሔዋን አይደል ወይ… ያጎታችን ደሙ…››

እንኳን ባያታችን ይቅርና በአዳም<br>
እንኳን በናታችን ይቅርና በሔዋን<br>
ባንተም አላዘንን… ባንተም አላዘንን…<br>
ሣንጠይቅ ፈጥረሽን… ስንጠይቅ ሥት ፈጨን፡፡…

በዚህ ሰዓት ከዮቤድ ዐይኖች ዕንባ… ወደ መሬት ሲንጠባጠብ… በጭፈራው መሃል በርጋታ… የምታስተውለው ‹‹ኑሄም›› ተመለከተች… ህብረ ቀለም ያለው ቀሚሷን በቀኝ እጇ.. ወደ ላይ… ሰብሰብ… አድርጋ… ወደ ሁዋላዋ… ዞረች… ዮቤድ ዕንባውን በእጁ ከጠረገ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከተው ውበት… ወደ ጥልቁ የሚወስደውን የእግርን ውበት ነበር… ያውም የኑሄምን እግር…

እንሆ በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ከኃዘኑ የሚጠገንበት ከሃዘኑ… የሚታከምበት ታላቁ ምስጢር ተገኘ… ሙዚቃ… ሴት… ውበት…

‹‹ወይንና ሙዚቃ ሴት ያላፈቀረ<br>
ዕድሜውን በሙሉ… ተሰቃይቶ ኖረ›› እንዲል ባለ ቅኔ

# የፓርላማ አሠራርና የፍትህ

... ከገፅ 4 የዞረ

በመሠረታዊነት እንግልቱ የሚቀረፈው በፓርላማ መድረክ ውይይት ስለተደረገ ብቻ ሳይሆን አገሪቷ በምታስመዘግበው ዕድገት፣ ለዜጐች በምትፈጥረው ስራና ከሌሎች አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት ሰጥቶ በመቀበል መርህ ላይ ሲመሰረት በመሆኑ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሳካ ምክር ቤቱ ሕግ በማውጣትና በቁጥጥርና ክትትል ስራ ላይ ተጠምዶ ይገኛል፡፡ እንግልቱና ውርደቱ በድህነቱ ምክንያት የተፈጠሩ ጠባሳዎች በመሆናቸው መሰረታዊ መፍትሄ የሚገኘውም በሚመዘገበው ዕድገት ልክ ስለሆነ የዜጎቻችን ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በም/ቤቱ ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የሚያሳዩት ምክር ቤቱ ምን ያህል ለዜጎች እንደሚያስብ ማረጋገጫ እንጂ ፍትሕ ጋዜጣ እንደሚለው ከዜጐች ብሶት ይልቅ የሌላ አገር ዜጐች መንከባከቡን የሚያሳይ እንዳይደለ ልብ ሊባል ይገባል፡፡

ሌላው ነጥብ የአሸባሪነት ጉዳይ ከመምህራን መከፋትና ከሃይማኖት ተከታዮች ብሶት ቅድሚያ አግኝቷል የሚል ነው፡፡ አሸባሪነት የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ቀንድ የአፍሪካ እና በአጠቃላይ የዓለም ስጋት በመሆኑ የፓርላማው ቅድሚያ አጀንዳ መሆኑ አያስወቅስም፡፡ በመሆኑም በሽብርተኝነት ዙሪያ እየመከረ ሕግ ማውጣቱና ውሳኔዎችን ማስተላለፉ ተገቢ ነው፡፡ በፍትሕ ጋዜጣ እምነት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል የተባሉት ጉዳዮችም ቢሆኑ በምክር ቤት አባላት በዕለቱ ተጠይቀው በቂ ማብራሪያ ከመስጠቱ በተጨማሪ ዘርፉን መሰረት በማድረግ የተደራጁትም ቋሚ ኮሚቴዎችም በጉዳዩ ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድርጋቸው ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ፍትሕ ጋዜጣ የም/ቤቱን አባላት ለመከፋፈል ሞክሯል፡፡ የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉንና ሌሎችን የምክር ቤት አባላት ለሁለት ከፍሎ ከጉራፈርዳ ከተፈናቀሉ ሰፋሪዎች ጋር ያያይዛል፡፡ ፍትሕ ጋዜጣ ጉዳዩ በፓርላማ መድረክ መነሳት የነበረበት ከምሥራቅ ጎጃም ተወክለው በመጡ ወይም ከአማራ ክልል በተመረጡ የፓርላማ አባላት እንጂ በተከበሩ አቶ ግርማ አይደለም ይላል፡፡ የዚህ ሀሳብ የሕግ መሰረቱ ምን ይሆን? የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 54 ንዑስ አንቀፅ 4 የምክር ቤቱ አባላት የመላው ህዝብ ተወካዮች እንደሆኑ ያስቀምጣል፡፡ ይህም በመሆኑ የፌዴራል መንግስትን የሚመለከት አንድ ጉዳይ በየትኛውም የአገሪቱ ክልሎች ቢፈጠር ማንኛውም የፓርላማ አባል ጉዳዩን በምክር ቤቱ ጉባኤ የማንሳት መብት አለው፡፡ በአንዱ ምርጫ ክልል የተፈፀመውን ጉዳይ የሌላ ምርጫ ክልል ተወካይ እንዳያነሳ የሚከለክል ሕግ ያለመኖሩ ማሳያው ማንኛውም የፓርላማ አባል በየትኛውም ክልል የተፈፀመውን ጉዳይ ጥያቄ የማንሳት መብት በመጠቀም በተጠቀሰው ቀን የተከበሩ አቶ ግርማ ጥያቄውን ማንሳታቸውና ከሕግ አንፃር አግባብነቱ ታምኖበት በቂ ምላሽ መሰጠቱ አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡ በአጠቃላይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠው ማብራሪያ የፍትሕ ጋዜጣ አዘጋጆችን ጨምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተደራሽ የተደረገ ስለሆነ ሃቁ ከሕዝብ ዘንድ የተደበቀ አይደለም፡፡ በፍትሕ ጋዜጣ አይን ሲታይ ማብራሪያው ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ የማይሆኑ ናቸው ብሎ ካመነ ያለመቀበል መብት ሆኖ ሳለ ሕገ-መንግስታዊ ሥልጣናቸውንና ተግባራቸውን በአግባቡ እየተወጡ የሚገኙትን የፓርላማ አባላት ክብርና መልካም ስም የሚነካ፣ ትክክለኛ ያልሆነና ሕግ ላይ ያልተመሰረተ ዘገባ በማውጣት ወቀሳ ማቅረብ ግን ተገቢ ያለመሆኑንና ፍትሐዊነት የጐደለው መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

# በእነውብሸት የይቅርታ ጉዳይ

... ከገፅ 1 የዞረ

የቀረበው አስተያየት ቀደም ብሎ ለሚመለከተው አካል የደረሰ ሲሆን የይቅርታው ጉዳይም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ በ14 ዓመት ፅኑ እስራትና በ33 ሺህ ብር፤ እንዲሁም ዘሪሁን ገ/እግዚአብሔር በ17 ዓመት ፅኑ እስራትና በ50 ሺህ ብር መቀጣታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ሆኖም በተመሳሳይ ወንጀል ከውብሸት ጋር ተመሳሳይ የእስራትና የገንዘብ መቀጮ የተቀጣችው፣ በቅርቡ የ2012 የአለም አቀፍ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን /IWMF/ ሽልማትን ያገኘችው እና የፍትህ ጋዜጣ ባልደረባ የነበረችው ርዕዮት አለሙ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ መጠየቋ ይታወቃል፡፡

# ጋሻና ጦሬን አምጣ ፈረሴን፤ እለውጣለሁ ላገሬ ነፍሴን።

ከሥነ ቃል የተወሰደ



ከታዴዎስ ታንቱ

ኢትዮጵያ! የሺህዎች ዓመታት የመንግሥት ሥርዓት ባለቤት፤ የአፍሪቃ ጉልላት፤ የዓለም በኩር ሀገር፤ የአንድነት ተምሳሌት፤ የጥቁር ጌጥ፤ ሉዓላዊት መሬት፤ ትናንት ለነፃነትሽ፤ ለአንድነትሽና ለሰላምሽ የተከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ በጉልበተኛ ገገርዎቻችን ተኰንኗል! ተወግዟል! ሉዓላዊነትሽ ከዕውንታ በተቃራኒ እውነት ተደርጎ ተሰብኳል! ሐቅሽ ከሐቅ ተለይቶ ወድቋል! ኢትዮጵያ ሀገሬ! ታሪክሽ በቀበሌኛ ልውስ አማርኛ ተረት! ተረት! የመሰረት! ወግ ተብሏል። የጀግኖችሽ አፅም በጆኒያ እንጦርጦስ ተወርውሯል። ክብር ለሙታን ተነፍጓል! ገንዘብ! ገንዘብ! ገንዘብ! የኢትዮጵያ ገዥዎች ዘፈን ሆኗል! ሕዝብ ተንቋል! ሥልጣነ ሕዝብ እንደማይታሰብ በድርጊት ታውጇል! ኃይል ሕግ ነው! ሕግም የአገዛዝ ኃይል ሆኗል! ሰፊው ሕዝብ ይማቅቃል! ሰፊው ሕዝብ ይሰደዳል! ስደት ደግሞ ይበረታታል! ደሃ ደግሞ መብላት ያምረዋል እንዴ? መልበስ ያምረዋል እንዴ? ቤት መሥራት ያምረዋል እንዴ? መኪና መግዛት ያምረዋል እንዴ? ደግሞ ደሃ መኻል ከተማ ውስጥ ምን ይሰራል? በል! መኻሉን ለቅቀህ ወደዳር ውጣ! ከተማው በሊዝ ተሸጧል! የውጭ ሀገር ሰዎች ይመጣሉ! በመኻል ከተሞች ውስጥ ደሃና አሮጌ ቤቶች አይኖሩም! ይህ የገዢዎች ድምፅ ነው!

ሀገሬ ኢትዮጵያ! አንቺ የመከራ ደሴት! የሰቆቃ ምድር! ዛሬም ለክብርሽ ቆመናል! ቀደምት ጀግና ልጆችሽን ዛሬም እናከብራቸዋለን እናደንቃቸዋለንም! አንድ! አንድ! አንድ! ቀጥል! ቀጥል! ቀጥል!

አስተካከለ! አነጣጠረ! ለቀቀበት! ድም! ድም! ድም! የብዙ ጀግኖችን ደም በግፍ ያፈሰሰ ባንዳ መትረየስ እንደ ጨበጠ ተደመሰሰ ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመትረየስ ተኳሽነት ተመድቦ እንደ ነበር ታውቋል። ለዚህ ከሞት ያነሰ ምን ይገባዋል? ተገቢውን ቅጣት በተገቢው ቦታ አግኝቷል። ታሪክ ይናገራል። ባንዳው በቅድሚያ የአርበኛውን አንገት በመትረየስ ቦድሶታል። በአፀፋ ተኩስ ግን ባንዳው ከትቢያ ጋር ተዋህዷል። መትረየስ እያንጣጣ አርበኛው በጠብመንጃ አንስቶታል። ጀግና መች ቀጠሮ ይሰጣል? የታሪክ ጨዋታ እንዲህ ነው! ይህ ሁነት ተመዝግቧል። ታሪክን በታሪክ ዓይን አይተናል። አሁን የምንገኘው በቀጥታ በትግራይ ክፍለ ሀገር በደጋ ተምቤን ጦር ሜዳ ላይ መሆኑ ይመዝገብልን። ጀግኖች ወድቀዋል። አንዳንዶች በከባድ ሁኔታ ቆስለዋል። ጀግናው የጦር ሰው ይግዛው ጠቦ በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት በመዋጋት ላይ ይገኛል። ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ጥቅምት 1928 ዓ.ም.

ጀግናው ተኳሽ ይግዛው ጠቦ በደጋ ተምቤን ጦር ሜዳ ኀሕ ሲቀድድ አንሥቶ ቀኑን ሙሉ ተዋግቷል። በዕለቱ የኢትዮጵያ ጀግና ቆሞ እየፎከረና እያቅራራ ሲዋጋ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን በምሽግ ራሱን ቀብሮ ሲተኩስ ውሏል። ኀሕ ሲቀድድ የተከፈተ ጦርነት ፀሐይ ስትጠልቅ ቆሟል። የጀግና ውሎ በመስዋዕትነት ታሪክ ለትውልድ በቅብብሎሽ ይደርሳል። ይህ የታሪክ ድምፅ ነው። ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅ የተቦደሰ አንገቱን ቀኑን ሙሉ በጨርቅ እንኳን አላሰረውም። አመቺ ሁኔታ አልነበረምና። ሲመሽ ግን ቁስሉ በጨርቅ ተሸፈነለት። የጀግና ውሎ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ሞት ወይም ነፃነት!

ቆራጡ ተኳሽ ይግዟው ጠቦ አሁን በዓቢይ አዲ ውጊያ ወረዳ ገብቷል። ጦርነት ተከፍቷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከአይሮፕላን ቦምብ በማዝነብ ላይ ይገኛል። በምድርም ያለ የሌለ ኃይሉን አሰማርቷል። ተናዳፊዎቹ የኢትዮጵያ ጀግኖች በርትተው ተዋግተዋል። ሆኖም በወገን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በተሰዉት ምትክ ሰው የግድ አስፈልጓል። ማግኘት ግን አልተቻለም። በዚህ ምክንያት ዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የበላይነት ሊሰማው ችሏል። የጥቁር አናብስት አቅም ለጊዜው ተዳክሟል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን እንደ ሽንፈት ቆጥሮታል።

ለእናት ሀገሩ መተኪያ የሌለውን ሕይወቱን ለመስጠት ቆርጦ የተነሳው ይግዛው ጠቦ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መምጣቱን ሰምቶ ወደ ትግራይ የዘመተው ጓንዴና ቤልጅግ ጠብመንጃዎችን ይዞ እንደ ነበር ለማወቅ ተችሏል። ከመነሻው ከራሱ ጋር ሰላሣ ሰዎች ብቻ እንደነበሩ ተመልክቷል። ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጋር ዋናው ጦርነት ከመካሔዱ በፊት በመንገድ ላይ ከባንዳዎች ጋር ጦርነቶችን አድርጓል። በየቦታው ድሎችን አስመዝግቧል። ታሪክ ዓይን አለው። አይቶታል። ታሪክ አፍ አለው። ይናገራል። ታሪክ እጅ አለው። ፅፎታል። እውነት ሐሰት ሊሆን አይችልም! ሐሰትም በይዘቱ ይቆማል!

ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ይግዛው ጠቦ መጋቢት 6 ቀን 1928 ዓ.ም. ከትግራይ ወደ ጋይንት ተመለሰ። ወኔው አልቀዘቀዘም። በቁርጠኝነቱና በዓላማ ፅናቱ ላይ ጥያቄ አልተነሳም። ጀግኖቹ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን በአድዋ የጦር ሜዳ አሳፍረው የመለሱት ጣሊያን እንዴት ደፈረን? የቁጭትና የእልህ ጥያቄ ዘወትር ያነሳል። አካሉ ግን በጣም ተጎድቷል። ከአምሥት ወራት በላይ በትግራይ ውስጥ ቆይቶ ተመልሷል። ልብሱ እላዩ ላይ አልቋል። ቁስሉም አልዳነም። ምንም ህክምና አልተደረገለትም። ጀግናው ይግዛው ጠቦ የተደራረቡ ችግሮች ቢፈታተኑትም በአቋሙ ፀንቶ ተገኝቷል። ለጥቂት ቀናት ዕረፍት አድርጓል። ከጓደኞቹ ተወያይቷል። የቁርጥ ቀን ልጆች ቆረጡ። ቆፍጣናው ይግዛው ጠቦ ጓደኞቹን ይዞ አዩ ወደተባለ በረሓ ገባ። ነገር ግን ሰላዮች በክትትል ጠመዱት። እንዴት ይንቀሳቀስ?

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፤
አስቀድሞ መግደል አሾክሿኪውን ነው።

በተለይ አየለ መንገሻ የተባለ የጣሊያን የሹመት ተስፋኛ ይግዛው ጠቦንና ጓደኞቹን መውጫ መግቢያ አሳጣቸው። ስለዚህ ጀግኖቹ ዕውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ለመደምሰስ የውሳኔ አቋም ወሰዱ። በአስቸኳይ ገቢራዊ ሊሆን ይገባል። በተግባራዊ እንቅስቃሴ ሒደት በጀግኖቹ ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ታስቧል። የጥንቃቄ ስልት ተቀይሷል። ቀን ተቆርጧል። ባንዳው አየለ መንገሻ ምሽግ አልነበረውም። ከመሰሎቹ ጋር መስክ ላይ ይውላል። ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መረጃ ይመግባል። በቤተክርስቲያን፤ በገበያ፤ በለቅሶ ቤትና በሠርግ ላይ እየተገኘ ወሬ ይሰበስባል። አሁን ግን መሞቻው ተቃርቧል። ጀግኖቹ እነይግዛው ጠቦ ፊት ጊዮርጊስ በተባለ ቦታ ይጠብቁታል። አልሰሜን ግባ በለው! በፍፁም አልጠረጠረም። ከግብረ አበሮቹ ጋር እየተግተለተለ መጣ። ጀግኖቹ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ዳቦ በማር የሚገምጡበት ሰዓት ደርሷል። ድምምምም! የሩምታ ተኩስ! አየለ መንገሻና ግብረ አበሮቹ ተደመሰሱ! የምሥራች!

ጀግናው ይግዛው ጠቦ ከጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ባንዳውን አየለ መንገሻንና ግብረ አበሮቹን ከደመሰሰ በኋላ በነበረበት በረሐ ውስጥ አልቆየም። የግድ ቦታ መቀየር ነበረበት። ስለዚህ ወደ ሌላ ቦታ አመራ። ምሽግ አበጀ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሳይመጣበት ግን ቀናት ሔዱ። በዚህን ጊዜ ይግዛው ጠቦ ቦዝኖ መቀመጥን እንደ ነውር ቆጠረው። እንዴት ሊሆን ይችላል? የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን ለቅቆ ሳይወጣ ዕረፍት አይታሰብም። ስለዚህ ከበረሐ ጓደኞቹ ጋር ውይይት አካሔደ። የውሳኔ አቋም ተወሰደ። የምን በረሐ ውስጥ መሽጎ መቀመጥ ነው? ወደ ጋይንት ወጡ። ሆኖም ከሕዝብ ዕይታ ተደበቁ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ የነበረበትን ቦታ ለማግኘት ግን ብዙ አልተቸገሩም። የምሽጉን አቀማመጥ በውል አጥንተዋል። ከጥቃት በኋላ የሚያፈገፍጉበትን አቅጣጫም በስምምነት ይዘዋል። ቀጥሎ ተግባራዊ እርምጃ ተፈጻሚ ይደረጋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅ የሆነው ጀግናው ይግዛው ጠቦ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ላይ ከቀን ጦርነት ይልቅ የሌሊት ጥቃት የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ሐሳብ አቀረበ። ባነሰ መስዋዕትነት የላቀ ድል ይፈለጋል። ይህን ማን ይጠላል? ፀሐይ ጠለቀች። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በአቅራቢያው ሽፍታ ለመኖሩ መረጃ አልደረሰውም። ለጊዜው ስጋት የሚሆን ኃይል አላሰበም። አሁን መሽቷል። ውድቅት ሆኗል። ውስን የጥበቃ አባላት ተመድበዋል። ከጥቂት ሰዓታት እንቅስቃሴ በኋላ ግን ሁሉም ገብተው ተኙ። ጀግናው ይግዛው ትዕዛዝ አውርዷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ይታጨዳል። የሬሣ ነዶ ይታሰራል። የጣሊያን መቃብር ተምሷል። የባንዳ ዕድሜ ያጥራል። በዚች ሌሊት! በዚህች ውድቅት! ሞት አይቀርም! ጀግና በአካል ይሞታል። በታሪክ ለዘለዓለም ሕያው ይሆናል። ልበ ሙሉ ሰው ይግዛው ጠቦ አሁን ወደ ፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ ተቃርቧል። ተከታዮቹም የተመደበላቸውን ቦታ ይዘዋል። ጠብመንጃ እንዳይተኮስ የሁሉም ቃል ነው። ቦምብ ይወረወራል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ዕንቅልፍ ወስዶታል። ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! አራት ቦምቦች ተወረወሩ። የአፀፋ ተኩስ አልተሰማም። ጥቂት የሚያጣጥሩ ጣሊያኖች ተስተዋሉ። ጊዜ ግን አልተሰጣቸውም። ጀግናው ይግዛውና ተከታዮቹ ከምሽጉ ውስጥ ገብተው በጎራዴ ጨፈጨፏቸው። ወሬ ነጋሪ እንኳን አልተረፈም። የተማረኩ መሣሪያዎችን ይዘው መንገዳቸውን ቀጠሉ። ከኢትዮጵያ ጀግኖች የተጎዳ አልነበረም። አኩሪ ድል! ድል! ድል!

ጀግናው የጦር ሰው ይግዛው ጠቦና ተከታዮቹ በመቀጠል ወደ አሞራ ገደል አመሩ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከጎንደር ተንቀሳቅሷል። በጣም የተጠናከረ ኃይል እንደነበረ ተመልክቷል። ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች ግን እንደ ተለመደው ኋላ ቀር መሳሪያ ይዘዋል። በሰው ኃይልም ብዙ አልነበሩም። ሆኖም ለማፈግፈግ አልፈለጉም። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተቃርቧል። የኢትዮጵያ ጀግኖችም ጥናፉ በተባለ ቦታ መሽገዋል። የፈለገው ኃይል ይምጣ! ሽሽት አይታሰብም! መማረክም ሞት ነው! በለው! በለው! ድም! ድም! ቡም! ቡም! በገዛ ሀገሬ ለባዕድ አልገዛም! ይህ በአሞራ ገደል የኢትዮጵያ አርበኞች ድምፅ ነው! በሺህ የሚገመቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አባላት ተገደሉ። ከኢትዮጵያ ጀግኖችም ብዙ አርበኞች ተሠውተዋል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ፈረጠጠ። የአርበኞች ድል አድራጊነት ተበሰረ። በጣም ብዙ የጦር መሣሪያ በምርኮ ከአርበኞች እጅ ገብቷል። ይህን ሁሉ መሳሪያ ምን ያደርጉ? ተመካከሩና ገሚሱን ለገበሬዎች አስታጠቁ። ገበሬው በጦርነቱ ሰዓት ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ ተደስተዋል። እህልና ውኃ አቅርቧል። ቁስለኞችን ረድቷል። የሞቱትንም ቀብሯል። የተጠበቀባቸውን አስተዋፅኦ ሁሉ አድርገዋል።

በቆፍጣናው ተዋጊ በጀግናው ይግዛው ጠቦ የተመራው የአርበኞች ኃይል በመቀጠል ወደ ደብረ ታቦር አቅንቷል። የአንድ ቀን ዕረፍት እንኳን አልነበረም። በፋርጣ፤ በጨጨሆ፤ በአፈር ገማኝና ደራ መስቀል በተባሉ ሥፍራዎች ከፍተኛ ጦርነቶች ተካሔዱ። በተለይ በፋርጣ ላይ የኢትዮጵያ አርበኞች በጎራዴ ገብተዋል! ጣሊያንና ባንዳን አነባብረው ጥለዋል። ሬሣ ከምረዋል። በጎራዴ ሸረካክተዋል። የጀግና ውሎ በጀግና ተግባር በታሪክ ይህን ይናገራል!


በቁርጠኛው አርበኛ በይግዛው ጠቦ የተመራው የወገን ኃይል አሁን በወገራ በኩል ሄዶ ኮሰየ ከተባለ መንደር ደርሷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መሽጎ ይጠባበቃል። አርበኞች ተጠግተዋል! ተጠግተዋል! ተጠግተዋል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተኩስ ከፈተ! እንደማይቀርለት አውቋል! አርበኞች አፀፋ መልሰዋል! ጦርነቱ ተፋፍሞ ቀጥሏል! ቀኑን ሙሉ ጀግና ሲጥልና ሲወድቅ ውሏል! አሁን እየመሸ ነው! አርበኞች በጨበጣ ገብተዋል። በሒደቱ አንዲት ጥይት የይግዛው ጠቦን ጉንጭ በስታ ወጣች። ብዙ ደም ፈሰሰው። ደክሞት ወደቀ። ቁስሉን በእሳት ለኰሱለት። አሁን መሽቷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ፈርጥጧል። ድል የአርበኞች ሆኗል። ታሪክ ነቃሽ ነው! እውነት ይቀበራል! ግን አይበሰብስም!

በጀግናው አርበኛ በይግዛው ጠቦ አመራር አሁን የወገን ኃይል ወደ ደምቢያ ተንቀሳቀሰ። በተለይ ድርማ በተባለ ሥፍራ የወገን ተዋጊ ኃይል ጣሊያንን ከአፈር ጋር አዋህዶታል። እንዲሁም በቁልቋል በር መሽጎ የነበረውን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አርበኞች እንዳልነበረ አድርገዋል። በተመሳሳይ መልኩ በሳሙና በር አድፍጦ የነበረውንም አጨዱት። መነጠሩት። አሁን ወደ 1933 ዓ.ም. ገብተናል። የዓለም ሀገራት የኃይል አሰላለፍ ተቀያይሯል። ኢትዮጵያ ወታደራዊ ድጋፍ በተግባር አግኝታለች። አርበኞችም በርትተዋል። የአርማጭሆ፤ የጋይንትና የበለሳ አርበኛ እየፎከረ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን እስከ አዘዞ አሳደደው። ደመሰሰውም። በመጨረሻ ጄኔራል ናዚ ብቻውን ቀረ። ጥቂት ቆይቶ ጎንደር ከግፈኛው ወራሪ ኃይል በአስተማማኝ ደረጃ ፀዳች። የጀግናው የይግዛው ጠቦና የመሰሎቹ ተጋድሎ ፍሬ አፍርቷል። የጀግኖች ደም በከንቱ አልቀረም። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመላው ኢትዮጵያ በምርኮ ተያዘ።

ቆፍጣናው ተኳሽ ይግዛው ጠቦ በአምሥቱ ዓመታት በ48 የውጊያ ወረዳዎች በአመራርና በተዋጊነት ተሳትፏል። 5 ጊዜ በከባድ ሁኔታ ቆስሏል። ይህ ጀግና ከድል በኋላ የጉስቁልና ሕይወት መርቷል። የመከራ ኑሮ ገፍቷል። በዘውዳዊው አገዛዝ ተጠልቷል። ለሰበቡ ሰበብ አልጠፋም። በአምሥቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ዓመታት ከልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ጋር ግንኙነት ማድረጉ እንደ ምክንያት ተመዝግቧል። እንዴት አንድ የኢትዮጵያ ጀግና በዚህ መናኛ ምክንያት ተገቢውን ከበሬታ ያጣል? በነገራችን ላይ ቴዎድሮስና ዮሐንስ በአምስቱ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ዓመታት በአርበኝነት የታገሉ የልጅ ኢያሱ ልጆች እንደ ነበሩ አንርሣ! የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ለበርካታ ባንዳዎች ሹመትና ስልጣን እንደ ሰጠ ይታወቃል። ታዲያ በጀግናው ይግዛው ጠቦ ላይ ምን አየበት? አርበኝነት ወንጀል ነው? ኢትዮጵያ የግፍ ሀገር! ዝንተ ዓለም አድርባዮችና አፈጮሌዎች ተንደላቅቀው የሚኖሩባት ሀገር! ኢትዮጵያ የግፍ ሀገር! ዛሬም ግን እንወድሻለን! ለክብርሽ ዘብ ቆመናል! እናታችን ነሽና! ጀግናው ይግዛው ጠቦ በየካቲት ወር 1980 ዓ.ም. በሕይወት እንደነበረ ታውቋል። ዕድሜው በዚያን ጊዜ 76 ዓመት ነበር። ዓይኖቹ ሊጠፉ ተቃርበዋል። ማዕረጉ ከግራዝማችነት አላለፈም። ለማስመሰል ያህል ኒሻንና የወርቅ ሜዳይ ተሰጥቶታል። ነገር ግን በጥላቻ ዓይን ሲታይ ኖሯል። ይህ ጀግና አሁን በሕይወት ይኖር ይሆን? ምናልባት ሞቶ ይሆን? የጀግና አቀባበርስ ተቀብሮ ይሆን? መቃብሩስ ልማት ገለመሌ ተብሎ ተቆፍሮ አፅሙ በጆኒያ የትም ተጥሎ ይሆን? ልጆች አሉት ይሆን?

ጋሻና ጦሬን አምጣ ፈረሴን፤
እለውጣለሁ ላገሬ ነፍሴን።

አዲስ መፅሐፍ በገበያ ላይ




በሁሉም የመፅሐፍት መደብር ይገኛል

## በሰሜን ጐንደር ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ ከሁለት ሺህ በላይ ገበሬዎች ከእርሻ መሬቶቻቸው ተፈናቅሉ ተባለ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጐንደር ዞን ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳ የሚኖሩ ከሁለት ሺህ በላይ ገበሬዎች ለአመታት እያረሱ ከሚያለሙት የእርሻ መሬታቸው በተለይ ከባለፈው ወር ጀምሮ በኢንቨስትመንት ሰበብ መፈናቀላቸውን የፍትህ ምንጮች ገለፁ፡፡

ከስድስት እስከ አስራ አምስት ዓመት ያህል እንደያዙት የእርሻ መሬት ስፋት መጠን ለመንግስት ተገቢውን ግብር በመክፈል መሬታቸውን በማልማት ይተዳደሩ እንደነበረ የሚናገሩት እነኚህ ገበሬዎች፣ የማፈናቀል ሂደቱ ከጀመረበት ከሶስት ወራት ወዲህ በአጠቃላይ መፈናቀላቸውን ምንጮች ያስረዳሉ፡፡ ለገበሬዎቹ መፈናቀል ዋናው ምክንያትም ከሌላ አካባቢ ለመጡ የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገራት ኢንቨስተሮች መሬታቸው መሰጠቱ ነው፡፡

‹‹ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ለመሬቱ ውል አልያዛችሁም ተብለናል፡፡ እኛ ደግሞ ውል ያልሰጣችሁን እናንተ ናችሁ የሚል መልስ ስንሰጣቸው ከአሁን በኋላ ለአዲስ ሰው እንጂ ለሌላ ለነባር አንሰጥም ተባልን›› የሚሉት አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የአካባቢው ነዋሪ ‹‹እየተሰራ ያለው ስራ ይዘገንናል›› በማለት ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

‹‹እህል አብቃይና እህል የማያበቅል መሬት›› እየተባለ እንዲጠቀሙ ለተፈለጉ አካላት ጥሩ ቦታ፣ እንዲጠቀሙ ላልተፈለጉት ደግሞ ለእርሻ ስራ የማያመች መሬት ተለይቶ መስጠቱን ምንጮች በሃዘኔታ አስረድተዋል፡፡

ለአመታት ተገቢውን ህጋዊ ግብር የሚከፍሉበትን የእርሻ መሬት እየተነጠቁ ለባለሃብቶችና ለኢንቨስተሮች ሲሰጥ በተባለው መሰረት ምትክ ቦታ እንዳልተሰጣቸው ገበሬዎቹ ገልፀዋል፡፡

ለችግራቸው መፍትሄ ለማግኘት የሰሜን ጐንደር መስተዳድር ጋር በተደጋጋሚ በመመላለስ የመስተዳሩ ኃላፊ የሆኑትን አቶ ግዛው አማረን ቢያነጋግሩም ‹‹አሁን ምንም እንዳትናገሩ፣ ሄዳችሁ ወረዳቸውን ጠየቁ›› የሚል መልስ ማግኘታቸውንና ወረዳውም ‹‹ዞኑን ጠይቁ›› እንዳላቸው ስማቸው እንዳይጠቀስ ያልፈለጉት የአካባቢው ነዋሪ ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

‹‹የዘንድሮ እርሻ ሊጀምር የቀረው ሶስት ወር ነው፡፡ ግብር ከምንከፍልበት መሬት ተፈናቅለናል፡፡ የአርማጭሆ ህዝብ እየተፈናቀለ ይገኛል፡፡ ህብረተሰቡ ከቀየው ከተነቀለ የት ሊሄድ እንደሚችል ማሰብ ነው›› በማለት ተፈናቃዮች ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም ፍትሃዊ የሆነ የመሬት ክፍፍል ሊያገኙ እንደሚገባና አድሏዊ ስራ መስራቱ ሊቆም እንደሚገባ ያስገነዘቡት ምንጮች ‹‹የሚመለከተው አካል ለችግራቸው አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጠንና መሬታችንን ሊመልስልን ይገባል›› በማለት በምሬትና በሀዘን ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

የፍትህ ዘጋቢም ጉዳዩ ወደሚመለከተው ወደ ሰሜን ጐንደር አስተዳደር ቢሮ ስልክ ብንደውልም የቢሮው ስልክ ስለማይመልስ ምላሻቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡

## ከመላው ዓለም የተመረጡ አርቲስቶች በለንደን ኦሎምፒክ ፌስቲቫል ላይ እንዲገኙ ተጋበዙ

## -ከኢትዮጵያ በዕውቀቱ ሥዩም ተጋብዟል

ፖኤትሪ ፓረነስስ የተባለ የእንግሊዝ መንግስት የባሕል ማዕከል የአለም አቀፍ ኪነ-ጥበብ መስፈርትን ያሟላሉ ያላቸውን ሁለት መቶ ደራሲያን፣ ገጣሚያንና ሙዚቀኞችን በክረምቱ የለንደን ኦሎምፒክ የኪነ-ጥበብ ፌስቲቫል ላይ እንዲገኙ መጋበዙን ቢቢሲ ዘገበ፡፡

በፌስቲቫሉ ላይ ታላላቅ የፈጠራ ባለሙያዎች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ መካከል፣ የኖቬል ሽልማት አሸናፊው አየርላንዳዊው ሳሚውስ ሄኒ እንዲሁም የቀድሞ የሰሜን ኮርያ ፕሬዚዳንት የቤተመንግስት ገጣሚ የነበረና ስርዓቱ ኮብልሎ በደቡብ ኮሪያ ጥገኝነት የጠየቀው ጃንግ ጂን ሲዋንግ እንደሚገኙ ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

የባሕል ተቋሙ አምስት ሺህ ያክል እጩዎች የቀረቡለት ሲሆን በመጨረሻ ማጣሪያ ሁለት መቶ ያክሉን መርጧል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም ኢትዮጵያዊው ገጣሚ እና ደራሲ በእውቀቱ ስዩም ይገኝበታል፡፡ ፓኤትሪ ፓረነስም የበዕውቀቱ ሥዩምን ስራዎች በእንግሊዘኛ የናሙና ትርጉም ከገመገመ በኋላ ከተጋባዦች አንዱ አድርጐ መርጦታል፡፡ በፌስቲቫሉ ላይም በዕውቀቱ፣ ከታዋቂው ሴኔጋላዊው ሙዚቀኛ ባባ ማል ጋር በመቀናጀት የግጥም ስራውን እንዲያቀርብ መርሐ ግብር ተይዞለታል፡፡

እንደ ቢቢሲ ዘገባ ከሆነ በፌስቲቫሉ ላይ የተጋበዙ ገጣሚዎች ስራቸው በሄሊኮፍተር ይበተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግጥሞቻቸው “World record Anthology” በተሰኘ መድብል ውስጥ ይካተታሉ፡፡

## ኢቲቪ በ<<አኬልዳማ>> ዘገባው መቀጣት ይገባዋል ተባለ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ 5ተኛ ተከሳሽ በሆኑት አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ላይ በችሎት መድፈር ወንጀል የሰጠበት የውሳኔ መርህ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት (ኢቴቪ) ‹‹አኬልዳማ›› በሚል ባቀረበው ዘገባ ላይ የፍርድ ቤቱ አሰራር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደሩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ሲል የመላው ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ /መኢዴፓ/ ገለፀ፡፡

በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በቃሊቲ ማረሚያ ቤት በእስር ላይ የሚገኙት የመኢዴፓ ፓርቲ የስራ አስፈፃሚ አባልና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ‹‹ማቆሚና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ እንባ›› በሚል ርእስ በፍትህ ጋዜጣ ባስነበቡት ፅሁፍ ‹‹የፍርድ ቤትን ስርአት አጓድለሃል›› በሚል የስምንት ወር እስራት እንደተፈረደባቸው ያወሳው ፓርቲው ይህ የቅጣት ውሳኔ ‹‹አኬልዳማ›› በሚል ርእስ ኢቴቪ አቅርቦት ለነበረው አሉታዊ ዘገባም ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባ በ7/9/2004 ዓ.ም. በፓርቲው ዋና ፀሐፊና የምርጫ ጎዳዮች ሃላፊ በሆኑት በአቶ ዘመኑ ሞላ ተፈርሞ በወጣው መግለጫ ላይ አስታውቋል፡፡

በተያያዘም ፓርቲው ‹‹ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ያወጣውን አፋኙ የሳንሱር ህግ፣ ህገ-መንግስቱ የሰጠውን የመጻፍና የመናገር መብትን የጣሰ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ህግ ህገ-መንግስቱን የሚያፈራርስ ስለሆነ ባስቸኳይ እንዲቆም እና ማተሚያ ቤቱ ለህገ- መንግስቱ ተገዢ እንዲሆን እንጠይቃለን›› ሲል ለ ፍትህ በላከው መግለጫ አሳውቋል፡፡

## ባልቻ ሆስፒታል ለአትላስ ት/ቤት እርዳታ ሰጠ

ባልቻ ሆስፒታል በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ በተልምዶ ካራቆሬ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለሚገኘው አትላስ አፀደ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት ግምቱ አምስት ሺ አምስት መቶ አስራ አምስት ብር የሚያወጣ የሕክምና መገልገያ በእርዳታ መልክ ሰጠ፡፡

ትምህርት ቤቱ ለ3ኛ ጊዜ ከሆስፒታሉ የተደረገለትን እርዳታ ባለፈው ዓርብ በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ በመገኘት ከሆፒታሉ ዳይሬክተር ጄኔራል ማስተር አሌክሳንደር ብርየቭ መረከቡን የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በተለይ ለፍትህ ገለፀዋል፡፡ ት/ቤቱ በቅርቡ የተመሰረተበትን 10ኛ ዓመት በሚያከብርበት ወቅት የሆስፒታሉ ኃላፊዎች ክብረ በአሉ ላይ እንደሚገኙ ሀላፊዎቹ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

## <<ሕማማትና በገና>> እና <<የዳግማዊ ገፆች>> የተሰኙ መጽሐፍት ታተሙ

‹‹ሕማማትና በገና› የተሰኘው የታዋቂው ደራሲ አዳም ረታ መጽሐፍ ታተመ፡፡ መጽሐፉ 13 ያህል አጫጭር ልብ ወለድ ታሪኮችን የያዘ ሲሆን ዋጋውም 39 ብር ነው፡፡ ደራሲ አዳም ረታ ‹‹ማህሌት››፣ ‹‹አለንጋና ምስር››፣ ‹‹እቴሜቴ የሎሚ ሽታ››፣ ‹‹ከሰማይ የወረደ ፍርፍር››፣ ‹‹ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ›› እና ‹‹ግራጫ ቃጭሎች›› የተባሉ መጸሐፍት ደራሲ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በተያያዘ ዜና ‹‹የዳግማዊ ገፆች›› የተሰኘ የረጅም ልብ ወለድ መጽሐፍ ታትሞ ለንባብ በቃ፡፡ በአሸናፊ መለሰ የተደረሰው መጽሐፍ 224 ገፆች ያሉት ሲሆን በሁልም ምፅሃፍት መሸጫ መደብር ለገበያ መቅረቡን ደራሲው ለፍትህ ገልጿል፡፡

## አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ ያዘጋጀው የስዕል አውደ-ርዕይ እየተጐበኘ ነው

አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴዝ “High land landscape and reflection” በሚል ርዕስ ግንቦት 6 ቀን 2004 ዓ.ም. የከፈተው የሰዓሊ ፍጹም ተፈራና የሰዓሊ ለይኩን ወንዲፍራው ከ35 በላይ የስዕል ስራዎች የቀረቡበት ዐውደ ርዕይ እስከግንቦት 18 ቀን 2004 ዓ.ም. እንደሚቆይ አዘጋጆቹ ለፍትህ በላኩት ደብዳቤ ገለፁ፡፡

ዐውደ ርዕዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ዲፕሎማቶችና የስነ-ጥበብ ወዳጆች በተገኙበት የተከፈተ ሲሆን በስነ-ጥበብ ባለሙያዎችና አፍቃሪዎች እየተጐበኘ ይገኛል፡፡

## የመጨረሻው ቀሚስ እሁድ ይመረቃል

በሐየስ ፊልም ፕሮዲውስ የተደረሰው ‹‹የመጨረሻዋ ቀሚስ›› የተሰኘ ፊልም እሁድ ግንቦት 12 ቀን 2004 ዓ.ም. በጁፒተር ኢንተርናሽናል ሆቴል ቦሌ ቅርንጫፍ ይመረቃል፡፡

ሐኖ ፊልም ፕሮዳክሽን ‹‹ስላንቺ›› የተሰኘውን ፊልም ፕሮዲውስ ያደረገና ኢትዮጵያን ወክሎ በሆሊውድ ‹‹በምርጥ ዓለም አቀፍ የፍቅር ኮሜዲ›› ዘርፍ የተሸለመ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን የእሁድ የምርቃት ስነ-ስርዓት ከቀኑ 5:00 እስከ 9:00 ሰዓት እንደሚቆይ ታውቋል፡፡

## ወጣቷ ህይወቷ አልፎ ገደል ውስጥ ተጥላ እና በአውሬ ተበልታ ተገኘች

በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ በተለምዶው መገናኛ በሚባለው አካባቢ ማንነትዋ ያልታወቀ ሴት ህይወቷ አልፎ በአካባቢው በሚገኝ ገደል ውስጥ ተጥላ፣ እንዲሁም በአውሬ ተበልታ በትናንትው ቀን መገኘቷን የፍትህ ዘጋቢ በቦታው ተገኝቶ ለመመልከት ችሏል፡፡

30 ዓመት እንደሚሞላት የተገመተችው ይህች ወጣት ትናንት አስከሬኗ የተገኘ ሲሆን ግድያው መቼ እንደተፈፀመና አስክሬኗም መቼ በስፍራው እንደተጣለ የታወቀ ነገር የለም፡፡

በቦታው የተገኘው የፍትህ ዘጋቢም አስክሬኑ የቆየ መሆኑን ለማየት የቻለ በመሆኑ ከፊል የሰውነት አካሏ በአውሬ መበላቱን አረጋግጧል፡፡

ዘጋቢውም ስለሟቿ የበለጠ መረጃ እንዲሰጡት በአካባቢ የነበሩትን የፖሊስ አባላት ቢጠይቅም ፖሊሶቹ ‹‹ገና ነው… ምንም ስላላወቅን መረጃ ልንሰጥ አንችልም፡፡›› በማለታቸው ያደረገው ሙከራ አልተሳካም፡፡ ለህትመት እስከገባንበት ሰአት ድረስ ማንነቷን የሚገልፅና ዘመድ ነኝ ብሎ የመጣ አካል አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅትና በአሳታሚዎች መካከል ዛሬ ውይይት ይደረጋል

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በቅርቡ ባወጣው ‹‹የህትመት ስራ ስታንዳርድ ውል›› ላይ አሳታሚዎች ‹‹ውሉ በቀጥታ ህገ መንግስቱን የሚንድ ነው›› በሚል ከፍተኛ ተቃውሞ በማንሳታቸው፤ የማተሚያ ድርጅቱ ኃላፊዎች እና አሳታሚዎች በድጋሚ ዛሬ ውይይት ያደርጋሉ፡፡

የማተሚያ ቤት ድርጅቱ ያወጣውን ውል በድርጅቱ ስር የሚያሳትሙ ሁሉም የጋዜጣ ድርጅቶች ‹‹ቅድመ ምርመራ›› በማለት ክፉኛ እየተቹትና እየነቀፉት ይገኛሉ፡፡

አሳታሚዎቹ ከትናንት በስትያ ተገናኝተው ውይይት ያደረጉ ሲሆን፣ በዚህ የጋራ ውይይት ላይም ዛሬ ከብራሃናና ሰላም ማተሚያ ቤት ጋር በሚደረገው ውይይት ላይ በሚቀርቡ ሃሳቦች ዙሪያ ተወያይተው የጋራ አቋም እንደያዙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ባለፈው ሳምንት ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊም ብራሃናና ሰላም ማተሚያ ቤት ያዘጋጀውን ‹‹የቅድመ-ምርመራ ውል›› እንዲሰርዝ በማድረግ ህግ-መንግስቱን የማስከበር ኃላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድ በደብዳቤ ጠይቀው መልስ እየተጠባበቁ እንደሆነ ይታወሳል፡፡

የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪ ተቋም የሆነው ሲፒጄም ባለፈው ሳምንት ውሉን ‹‹ቅድመ-ምርመራን ሕጋዊነት ማልበስ ነው›› በማለት በተቋሙ የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ቶም ሮድዮስ አማካኝነት ተግባራዊ እንዳይሆን መቃወሙ ይታወቃል፡፡

## አንድነት የስነ ጥበብ ባለሙያዎች የሚመሩት የውይይት መድረክ አዘጋጀ

ለመጀመሪያ ጊዜ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ የተዘጋጀው የስነ-ጥበብ ውይይት ላይ በርካታ የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች እና የስነ-ጥበብ አፍቃሪዎች እንደሚሳተፉ አዘጋጁ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ለፍትህ አስታወቀ፡፡

‹‹ስነ-ጥበቡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሚና›› በሚል የተዘጋጀው የመወያያ መድረክ ላይ ‹‹ስነ-ጥበቡ በህዝቡ ዘንድ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዳለው እና ስነ-ጥበብ ህብረተሰቡን መቅረጫ መሳሪያነቱን በሚገባ እየተገለገልንበት ነው¬¬? አይደለም? የሚለውን›› ለመገንዘብ እንደሚረዳ ፓርቲው ገለጿል፡፡

ፓርቲው ግንቦት 12 ቀን 2004 ዓ.ም በብሄራዊ ቲያትር አዳራሽ የሚከፈተውን የውይይት መድረክ የሚመሩት አንጋፋ የስነ-ጥበብ ባለሙያዎች ሲሆኑ ‹‹ስነ-ጥበቡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ሚና›› በሚል ጭብጥ ላይ ተንተርሰው ሀሳባቸውን በማንፀባረቅ፣ ተሳታፊዎችን በማወያየት፣ የተሳተፈውን ጥያቄ በመመለስ ውይይት እንደሚያደርጉ እና ውይይቱም ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 6፡00 ሰዓት እንደሚካሄድ የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

የህዝብ ግንኙነቱ ‹‹ስነ-ጥበብ በሀገራችን በእውነተኛ ባህሪዋ ጐልቶ እየወጣ አይደለም፡፡ ስለዚህም በእውነተኛ ባህሪዋ አልተጠቀምንባትም፡፡ እውነተኛ ባህሪዋ እንዲወጣና እንድንጠቀምበት ምን ማድረግ አለብን? የሚሉትን ጠንካራ ሀሳቦች በማንሳት ባለሙያዎቹ ማብራሪያና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ይጠቁማሉ›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የውይይት መድረኩን በአወያይነት ሰአሊና ቀራፂዎች፣ ደራሲና ፀሐፊ-ተውኔቶች እና ከተለያዩ የስነ-ጥበብ ሙያ ማህበራት የተጋበዙ ሙያተኞች እንደሚመሩት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተያያዘም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ግንቦት 28 ቀን 2004 ዓ.ም ለሚያደርገው ገንዘብ ማሰባሰቢያ የእራት ግብዣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ የካርድ ሽያጭ መሰብሰቡን የፓርቲው ም/የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ አቶ ፀጋዬ አላምረው በተለይ ለፍትህ ገለፁ፡፡

ፓርቲው እስከ አሁን በተደረገው የካርድ ሽያጭ ላይ ህብረተሰቡ ፓርቲውን ለመርዳት ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን ጠቅሶ ህብረተሰቡ በዚህ ተሳትፎው ከቀጠለ ቀኑ እስከሚደርስ ድረስ ፓርቲው ካቀደው በላይ ገንዘብ እንደሚሰበስብ ኃላፊው አያይዘው ተናግረዋል፡፡

## ፕ/ት ኦባማ ነፃ ፕሬስ በምግብ ራስን ለመቻል የሚኖረውን ሚና አጉልተው እንዲሟገቱ ተጠየቁ

ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ‹‹ነፃ መገናኛ ብዙሃን የግብርና ተግዳሮቶችንና ድርቅን ለመታደግ ለሚጫወቱት እውነቱን የማሳወቅ ሚና እውቅና ሰጥተው ሊሟገቱ ይገባል›› ሲል ዓለማ አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ድርጅት /ሲፒጄ/ አስታወቀ፡፡

የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅቱ ረቡእ ግንቦት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. ለፕሬዘዳንት ኦባማ በላከው ደብዳቤ ላይ እንደገለፀው ‹‹ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ዕጦትን የአደጋ ደረጃ በማሳነስ፣ የነፃው ፕሬስ አባላት የምግብ ዕጦቱ ወደሚስተዋልባቸው አካባቢዎች ሄደው እንዳይዘግቡ በመከልከል እና ዘገባዎቻቸውን በቅድመ-ምርመራ በማጉደል የእርዳታ ሰጪ ሀገራትን እና የበጎ አድራጊ ተቋማትን ሚና አደብዝዛለች›› ሲል ወቀሳውን አሰምቷል፡፡

## በግንቦት 7 ክስ የዕድሜ ልክ ፍርደኛ … ከገፅ 1 የዞረ

ፖሊስ ኮሚሽን ሪፈራል ሆስፒታል ገብተው የህክምና ዕርዳታ በማግኘት መጋቢት 19/2004 ዓ.ም. ከሆስፒታሉ ወጥተው ወደ ማረሚያ ቤት ተመልሰው እንደነበረ እህታቸው ወ/ት መቅደስ ስንሻው ለፍትሕ ገልፀዋል፡፡

ከዚያም በድጋሚ ህመማቸው ጠንቶ ወደ ሆስፒታሉ የገቡት ፍርደኛው አቶ ክፍሌ ለ17 ቀናት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው አርብ ግንቦት 3/2004 ዓ.ም. ንጋት 11፡00 ሰዓት ላይ ህይወታቸው ማለፍን፣ አስከሬናቸውም በዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ምርመራ እንደተደረገላቸውና ቅዳሜ ዕለት በትውልድ መንደራቸው በባህር ዳር በምትገኘው ባህታማርያም ቤተክርስቲያን ቀብራቸው መፈፀሙን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በአስታማሚነት ከጎናቸው የነበሩት ወ/ት መቅደስ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም ‹‹ወንድሜ ሕመሙን አያውቀውም፡፡ እኔም ለማወቅ አልቻልኩም፡፡ ብዙ ጊዜ ራሱን ይስት ነበር፡፡ ነገር ግን በሆስፒታሉ ሊደረግለት የሚገባው ነገር ተደርጐለታል… ሞቱ ለእኛ በጣም ከባድ ጉዳት ነው፡፡ 11 ሰው ያስተዳድር የነበረ የቤተሰብ ኃላፊ ነው ያጣነው›› በማለት በጥልቅ ሀዘን ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

ፍትህ ጋዜጣም ስለአቶ ክፍሌ አማሟት ትክክለኛውን የህክምና መረጃ ለማወቅ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሪፈራል ሆስፒታል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑትን ዶ/ር ግርማ ሙሉጌታን በአካል አነጋግራቸው ነበር፡፡ ዳይሬክተሩም መረጃውን ለማግኘት በመጀመሪያ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ማሳወቅ እንደሚገባ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በዶ/ር ግርማ ምላሽ መሰረት በትናንትናው ዕለት ደብዳቤውን በማዘጋጀት በኮሚሽኑ የሚመለከታቸውን አካላት ለማነጋገር ፍትህ ጥረት አድርጋ ነበር፡፡ የፌ/ፖ/ዋ/ዳይ/ ስታፍ ዳይሬክተር የሪከርድና ማህተም ቲም መሪ ለሆኑት ረዳት ሳጅን ውሳኔ አማረ ደብዳቤውን ሰጥተናቸው ካዩት በኋላ ‹‹ኮሚሽነሩ አሁን የሉም፣ እሳቸው ማየት ስላለባቸው ለዛሬ አይደርስም›› በማለታቸው በድጋሚ ወደ ሆስፒታሉ ተመልሰን መረጃውን ማግኘት አልቻልንም፡፡

በተጨማሪም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ጊዜያዊ ኃላፊ የሆኑትን አቶ አዲሱ ጴጥሮስን ስልክ በመደወል ስለሟቹ የህመም ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ስንሞክር ‹‹አቶ ክፍሌ መሞታቸውንም አሁን ካንተ መስማቴ ነው፡፡ ክፍለ ሀገር ነው ያለሁት፡፡›› ካሉ በኋላ ሌላ ስልክ ሰጥተውን ነበር፡፡ የማረሚያ ቤቱ የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ምክትል ኦፊሰር ወደ ሆኑት አቶ በዛወርቅ ጥበቡ ስልክ ስንደውል ስልካቸው ባለመነሳቱ ምላሻቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡

አቶ ክፍሌ ‹‹በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ህገ መንግስቱን እና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል እና በትጥቅ አመፅ ለመጣል የጋራ ወንጀል አድማ ስምምነት በመፍጠር የወንጀል ድርጊቱን አላማ ውጤት እና ፍሬውን በሙሉ በመቀበል በማደራጀት በመምራት ስርዓቱን በሽብር እና በአመፅ ተግባር ለማፍረስ ተሳትፈዋል›› በሚል ከ45 ግለሰቦች ጋር በአምስት ክሶች ተከስሰው ጥፋተኛ መባላቸው ይታወሳል፡፡

ፍ/ቤቱም ታህሳስ 13/2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት 44 ተከሳሾችን በእድሜ ልክ ፅኑ አስራት እንዲቀጡ ከወሰነባቸው ግለሰቦች መካከል አንዱ የሆኑት አቶ ክፍሌ፣ በአማራ ክልል በጣና ሃይቅ ላይ የአስጐብኚ ድርጅት በግል ፍቃድ እንዲሰጥ፣ እንዲሁም ቡና ኢንተርናሽናል ባንክን በማደራጀት ውስጥ አንዱ የነበሩ ሲሆን የኢትዮጵያ የከበሩ ማዕድን ማሕበር ዋና ፀሐፊ ሆነው ማገልገላቸውም የግል ማህደራቸው እንደሚያስረዳ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ‹‹የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?›› (ማቴ.ወንጌል ም.16፥ቁ.13

እየሱስ ክርስቶስ ህዝቡን በተለያዩ ስፍራዎች እየተዟዟረ ያስተምር ነበር፡፡ በዚህም ብዙ ተከታዮችን ለማፍራት ቻለ፡፡ ከእርሱ ጋር አብረው ከነበሩት ሐዋርያት በተጨማሪም ብዙ የከተማው ህዝብ ውሎንና አዳሩን ከእየሱስ ጋር ያደርጉ ጀመር፡፡ በመንገዱም ወደ ቂሳሪያ ከተማ ሲደርስ ከእርሱ ጋር የነበሩትን ደቀ-መዛሙርቶችን ሰብስቦ አንዲት ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡

‹‹ጌታችን ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሳሪያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን›› የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?›› ብሎ ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም ‹‹መጥምቁ ዮሐንስ ነው የሚሉ አሉ፤ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርሚያስ፥ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት›› (ማቴ.ወ ም.16፥ቁ.13)

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ነገስታቶቻችን በህዝቡ ዘንድ ስለነበራቸው ተቀባይነት ብዙም ሲጨነቁ አይስተዋልም፡፡ ከዚህ ይልቅ የውጭ አገራት ህዝቦችና መሪዎቻቸው ስለእነርሱ በሚነግሯቸው ነገሮች፣ በሚቸሯቸው አክብሮቶች፣ በሚለግሷቸው ስጦታዎች ምክንያት እራሳቸውን አሳብጠው እንዲያዩ አድርጓቸዋል፡፡

አፄ ኃ/ስላሴ በነበራቸው ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የተነሳ በአለም ህብረተሰብ ዘንድ ስማቸው በእጅጉ ይነሳል፡፡ አብዛኛው አፍሪካ አገራት ከቅኝ ግዛት ባርነት ይላቀቁ ዘንድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የሞራል እርዳታ ከማድረግ ጀምሮ የጦር ስልጠናን እዚሁ አገራችን ላይ እንዲያገኙ ማበረታታትን ጨምሮ የጦር መሳሪያ እና የገንዘብ እርዳታን ያጠቃለሉ ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን አበርክተዋል፡፡ የቅኝ ግዛት ማብቃትን ተከትሎ በአፍሪካ አገራት ውስጥ የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶችን እልባት ለመስጠት የአገራችንን ወታደሮች ወደተለያየ የአህጉሪቱ ክፍል ልከው በሰላም ማስከበሩ ሂደት ሰፊውን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡ ተልዕኮው በአፍሪካ ብቻም የተገደበ አልነበረም፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ጥሪ ተከትሎ እስከዛሬ በታሪክ የሚዘከረውን ጀብዱ በኮሪያ ልሳነ-ምድር ወታደሮቻችን ሰርተው ተመልሰዋል፡፡

ንጉስነገስቱከጦርነትፖለቲካበተጨማሪም የአፍሪካ አገሮች የጋራ ህብረት ይመሰርቱ ዘንድ ዘርፈ ብዙ ሚና ተጫውተዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ በጎ ተግባራት በውጭው አለም ዘንድ በተለይ በአፍሪካ ‹‹የአፍሪካ አባት›› የሚል ስያሜን አስገኝቶላቸዋል፡፡ ዳሩ ምን ዋጋ አለው? ለእኛ ኢትዮጵያውያን ግን ንጉሠ ነገስቱ እንዲህ አልነበሩም፡፡ እርሳቸውም ‹‹ህዝቡ ስለእኔ ምን ይላል?›› የሚለውን ጥያቄ ጠይቀው አያውቁም፡፡ የሚሾምና የሚሽር የአገር ህዝብ መሆኑን ዘንግተውታል፡፡ የውጭ አገር ሰዎች ፍቅርና አክብሮት አቅላቸውን አስቷቸው፣ ከሰውም በላይ ሆነው መለኮታዊ ኃይል እንዳላቸው እየገለፁ ህዝባቸውን መስማትም ይመለኩ ዘንድ አስገደዱ፡፡ ይህም ሆኖ በመጨረሻዋ ሰአት ሳይቀር ራሱን ‹‹ደርግ›› በሚል የሰየመው የወታደሮች ስብስብ ‹‹እባክዎን ከዙፋኑ ገለል ይበሉ? ተራው የኛ ነውና›› ባለ ጊዜ እነዚያ ሁሉ አሞጋሾችና አጫፋሪዎች በስፍራው አልነበሩም፡፡ በጊዜውና በቦታው የነበሩት እርሳቸው ከቁብም ያልቆጠሯቸው ምስኪን ዜጎች ብቻ ናቸው፡፡

በጊዜው ይፈሩ የነበሩት ‹‹ስዩመ እግዚአብሔር›› በአንዴ ወደ ተራ ሰውነት ተቀየሩ፡፡ በአክብሮት ከፍ ዝቅ ይልላቸው የነበረው ህዝብም በትንሿ መኪና ውስጥ ሲመለከታቸው ‹‹ሌባ! ሌባ!›› እያለ አቀለላቸው፡፡ ህዝብን መዘንጋት ጊዜ ጠብቆ ያዋርዳልና የእርሳቸውም ፍፃሜ ይህ ሆነ፡፡

ደርግም ከንጉሱ ውድቀት አንዳችም ነገር ሳይማር በትዕቢት አገሪቷን ያሽከረክራት ጀመር፡፡ እንደቀደመው መሪ ሁሉ የውጭ ግንኙነትፖሊሲው ከገፅታ ግንባታ አንፃር እንደተጠበቀ ነበር፡፡ በጊዜው አለም ለሁለት ጐራ የተከፈለበት ወቅት በመሆኑ ከአንደኛው ጐራ የሚገኘውን ክብርና ሽልማት በመመልከት ብቻ ህዝቡ የሚሻውን ነፃነት በእጅጉ ነፈገው፡፡ ንጉሱ በአፍሪካ የጀመሩትን የሰላም ማስከበርና ፀረ-ቅኝ ግዛት ፖሊሲ ደርግም ቀጠለበት፡፡ በተቃውሞ ጐራ የተሰለፉትን ቡድኖች አቅርቦ አናግሮ መፍትሄ ከማበጀት ይልቅ የጦር መሳሪያ መፍትሄ ነው ብሎ ስላመነ በታሪካችን ዳግም ልናየው የማንሻውን አረመኔያዊ ድርጊት ፈፀመ፡፡ አንድም ቀን ሊቀመንበሩ ህዝቡ ስለእኔ ምን ይላል? ብሎ ተጨንቆ አያውቅም፡፡ ህዝቡ ያልኩትን ተቀበለ ወይንስ አልተቀበለም ከማለት ውጭ የህዝቡን ብሶትና እሮሮ የሚሰሙበት አንዳችም ትዕግስት አልነበራቸውም፡፡ በስተመጨረሻም ህዝብን ካለመስማት፣ ችግራቸውን ቀርቦ ካለመረዳት የሚመጣውን የውድቀት ማቅ ተከናነቡት፡፡ ህዝቡ አባረራቸው፡፡ አገራቸውን እንደናፈቁ ይኸው በስደት በሰው አገር ላይ ተጠልለው ይኖራሉ፡፡ የተቀሩት አጋሮቻቸውም የሃያ አመታት እስርን ተከናንበው በእስተርጅና የሚገባቸውን ክብር ተነፍገው ከህዝብ ጋር እንዳልነበሩ አሁን ከህዝብ ተነጥለው የፀፀት ጊዜን ከህሊና እረፍት የለሽ ጥያቄ ጋር እየገፉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህስ በላይ መራር ቅጣት ከየት አለ? ከህዝብ ወገን ያለመሆን እጣ ፈንታ ይህው ነው፡፡

ታሪክ እራሱን ይደግማል ይባላል፡፡ ዘመን በተሻገርን ቁጥር ካለፈው ስህተት መማር እስካልቻልን ድረስ የምንሄድበት መንገድ ተመሳሳይ ለመሆኑ አስረጂ አያሻንም፡፡ በዚህኛው ጉዳና ለሚጓዙ መሪዎች የትም ያህል እርቀት ይሂዱ እንጂ የሚደርሱበት የመጨረሻው የመንገዳቸው መዳረሻ ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

ተተኪው መንግስትም በህዝብ የተገፋውንና የተጣለውን ስርዓት ተክቶ የራሱንም የታሪክ ኃላፊነት ለመወጣት በመንበሩ ጉብ ካለ እነሆ ሃያ አመታት አለፉ፡፡ ኢህአዴግን ለዚህ ደረጃ ያደረሱት የደርግ መንግስት ደጋፊዎች አለመሆናቸው ይታወቃል፡፡ ህዝቡ የቀድሞ ስርዓት ባደረሰበት በደል ከመማሩ የተነሳ በከፈለው መስዋዕትነት የተገኘ የድል ፍሬ ነው፡፡ ኢህአዴግና መሪው በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ እራሳቸውን ከህዝቡ መነጠል ጀመሩ፡፡ ምን አልባት እንደአሁኑ የለየለት አይሁን እንጂ በፊትም ቢሆን ለህዝቡ የነበራቸው አመለካከት ከታሪክ ስህተት ለመማር አለመፍቀዳቸው አንዱ ማሳያ ነበር፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዙሪያቸው የነበሩትንና የህዝቡን ጩኸት የሚያስተጋቡትን ጠንካራ ግለሰቦች ቀስ በቀስ ከፖለቲካ ጨዋታ አፀዷቸው፡፡ በተቋውሞ ጐራም ሆነው መንበራቸውን ሊፈታተኗቸው የሚሞክሩትን ተቋማት እና ግለሰቦች ከፊቴ ገለል በሉልኝ አሏቸው፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጨዋታ ላይ ጫጫታ አያስፈልግም አሉ፡፡ ለህዝቡ እኔ ነኝ የማውቅልህ፣ የሌሎቹን አሉባልታ አትቀበል አፍራሽና መቼም የማይጠቅም ነው ሲሉ አወገዙ፣ ሆኖም ለፍላጎታቸው ያልተገዙትን (ከእነርሱ ጋር መሆን ያሻኛል) ያሉትን ግለሰቦች ከፀረ-ሰላሞቹ ጋር አብረው እንደሚደምሯቸው አስጠነቀቁ፡፡ ያሰቡትም ተሳካላቸው፡፡ ይህንን ማድረጋቸውን ካረጋገጡ በኂላ ፊታቸው እንደቀደሙት አባቶቻቸው ወደ ውጭው አገራት አዘነበሉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በአጠቃላይ አፍሪካ አገራት መካከል ‹‹አዋቂ መሪ›› ተደርገው እስከመቆጠርም እየደረሱ ነው፡፡ አፍሪካንም በመወከል በተለያዩ መድረኮች በመገኘት ስምና ዝናቸውን ከፍ አድርገዋል፡፡ የአፍሪካ ተራማጅ መሪ የሚል ተቀጥያ ስምም አተረፉ፡፡

ነገር ግን መፃህፉ ቅዱስ እንደሚነግረን ክርስቶስ ህዝቡን እያስተማረ ብቻ ቀጥ ብሎ ወደፊት የጀመረውን ጉዞ አልቀጠለም፡፡ ህዝቡ ስለእርሱ ምን ያስብ እንደሆነ ለማወቅ ይረዳው ዘንድ አረፍ ብሎ መጠየቅን ፈለገ፡፡ ግን ህዝቡ ስለእርሱ ያለውን አስተያየት አጥርተው ይነግሩት ዘንድ የፈቀደው እርሱ የሚበላውን በልተው፣ የሚጠጣውን ጠጥተው፣ በዋለበት ውለው ባደረበት የሚያድሩትን በመንፈስ እና በአላማ ፅናት እሱን የሚመስሉትን ደቀመዛሙርትን ነበር፡፡

መሪዎቻችን እንደ ዛሬው ትልቅ የስልጣን እርከን ከመርገጣቸው በፊት እንደ ማናችንም ተራ ሰው ነበሩ፡፡ ተራው ህዝብም ጋር በነበሩ ወቅት ባህሉን፣ አኗኗሩን፣ አስተሳሰቡን በደንብ ለመረዳት እድሉን አግኝተዋል፡፡ ህዝቡ ከመሪው የሚፈልጋቸውን ነገሮች ጠንቅቀው ይረዳሉ፡፡ ዛሬ ትንሽ ከፍ ሲሉ ወደ ታች የሚያዩት ህዝብ ስለእነርሱ በተራው ምን ያስብ እንደሆነ ለማወቅ ፍላጐት አላሳዩም፡፡ የተራው ህዝብ ብሶት ለእነርሱ ምንም አይደለም፡፡

በእርግጥ የአለም አቀፍ ህብረተሰብ ለመሪዎቻችን የቸረው ክብርና እንክብካቤ የአገሬውን ነዋሪ ይወክል ይሆን? የሚለውን ስናነሳ ማስተዋል ያለብን ክርስቶስ ‹‹የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?›› ብሎ ሲጠይቅ እራሱን ከአምላክነት መታወቂያው ክብር ስም ይልቅ ‹‹የሰው ልጅ›› የሚለውን ስያሜ ከመጠቀሙ ጋር ነው፡፡ ይህ ጥያቄም ህዝቡ የእርሱ፤እርሱም የህዝቡ መሆናቸውን በአንድም ይሁን በሌላ ለማሳወቅ የተጠቀመበት መሆኑን እንድንረዳ ይጥቁመናል፡፡

ክቡር ጠ/ሚኒስትር ሆይ፡- እስኪ በአጠገብዎ ያሉትን ሚኒስትሮች ስብስብ ያድርጉና ‹‹ህዝቡ ስለእኔ ምን ይላል?›› ብለው ይጠይቁ፡፡ ሐዋርያዎቹ ለክርስቶስ ‹‹መጥምቁ ዮሐንስ የሚሉ አሉ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ›› እንዳሉት እርስዎንም የተለያዩ ስያሜዎች እንደሚሰጥዎት እሙን ነው፡፡ ክርስቶስ ህይወቱን በሙሉ ለህዝቡ መልካም ነገርን ስላስተማረ ህዝቡ ስለማንነቱ የሰጠው ግምት በህይወት ዘመናቸው ለእስራኤል ህዝብ መልካም ነገርን አድርገው ያለፉትን የነቢያት ስም እየጠሩ ነው፡፡ የእኛስ መሪዎች ‹‹ህዝቡ ማን ይለናል?›› ብለው ቢጠይቁ ከማን ጋር አነፃፅረን ልንነግራቸው እንደምንችል እስቲ አስቡት፡፡ ለማንኛውም ህዝቡ ማን ይለናል ብላችሁ ጠይቁ! እናም መልሱን ተረድታችው በቅንነት ለመለወጥ እና ለመታረም ተነሱ፡፡ እነሆም ይህንን ለማድረግ ልቦና ይስጣችው፡፡ አሜን ይስጠን፡፡





